በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር አፈፃፀም ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን

# በተመለከተ የተከናወነ ሪፖርት















መጋቢት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ/ድርሞ/Executive Summary/ .... I

2. ክፍል አንድ .... 1

መግቢያ .... 1

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ራዕይ እና ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር .... 2

ራዕይ .... 2

ተልዕኮ .... 2

የኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር .... 2

ዓላማ .... 2

የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር .... 2

የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል .... 4

ድርጅታዊ መዋቅር .... 4

የሰው ኃይል .... 4

የፋይናንስ ምንጭ .... 4

የኢንስቲትዩቱ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DISCRIPTION) .... 5

የክዋኔ ኦዲቱ ዓለማ፡- .... 5

የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) .... 6

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡- .... 6

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁባቸው ማስረጃዎች .... 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡- .... 7

የኦዲቱ ወሰን .... 7

የኦዲቱ ዘዴ .... 7

3. ክፍል ሁለት .... 8

የኦዲት ግኝቶች .... 8

ኢንስቲትዩቱ ወቅታዊ መረጃና ግንዛቤ መስጠቱን በተመለከተ .... 8

ኢንስቲትዩቱ የሚሰጣቸውን የድጋፍ አገልግሎቶች ማሳወቁን በተመከተ .... 9

ኢንስቲትዩቱ የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ .... 10

ኢንስቲትዩቱ በቆዳና ቆዳ ውጤቶችዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ መደገፉን በተመለከተ .... 11

ኢንስቲትዩቱ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠናን መስጠቱን በተመለከተ ........13
በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ትስስር መፍጠርን በተመለከተ ........15
ኢንስቲትዩቱ የገበያ ጥናት፣ ማፈላለግና ትስስር መፍጠሩን በተመለከተ ........19
የማማከር አገልግሎትን በተመለከተ ........23
የምርትና የሰው ኃይል ልማት እና ምርምርን በተመለከተ ........25
ለጥሬ ቆዳ ግብዓት የሚደረግ ጥንቃቄን በተመለከተ ........29
በግብርና ሚኒስቴር የተሰራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ........31
የምርት እቅድ፣ ምርት ማምረት ሂደትና ጥራት ቁጥጥርን የማማከር አገልግሎት በተመለከተ...32
የላቦራቶሪ ፍተሻ ድጋፍን በተመለከተ ........34
የማሽን እና የባለሙያ እገዛን በተመለከተ ........35
ኤክስፖርት እስታንዳርድ የሆኑ የለሙ ምርቶችን ድጋፍ የሰጠ መሆኑን በተመለከተ ........36
የአካባቢ ብክለትን በተመለከተ ........38
የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ........42
የፍሳሽ ናሙና ምርመራን በተመለከተ ........44
የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራዎችን በተመለከተ........45
የኢንዱስትሪዎችን እድገት ለማፋጠን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ........45
ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ ........46
4. ክፍል ሶስት ........47
የመደምደሚያ ሀሳቦች ........47
የማሻሻያ ሀሳቦች........50
አባሪዎች ብዛት 4 ........1

## የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ/ድርሞ/Executive Summary/

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት በኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳና ቆዳ ውጤቶች የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ቀልጣፋ እና ውጤታማ አፈፃፀም ላይ ከ 2008 በጀት ዓመት እስከ 2010 በጀት ዓመት በተከናወኑ ተግባሮች የክዋኔ ኦዲት የተከናወነ ሲሆን የኦዲቱም ዓላማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ ዓለማ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 181/2002 በአንቀጽ 5 ዓለማ ስር ኢንስቲትዩቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዲስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት እንዳለበት የተመለከተ በመሆኑ ይህንንም ተግባር ለመወጣት በማቋቋሚያ ደንቡ በስልጣንና ተግባሩ ስር የተመለከቱትን ተግባራት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ባዘጋጀው የተገልጋዮች ቻርተር 19 የድጋፍ እና ክትትል አገልግሎቶችን ለመስጠት ባቀደው መሰረት በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ለተሰማሩ (የጫማ፣ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች እና የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ) ፋብሪካዎች በእቅዱ መሰረት ያከናወኑ መሆኑን መገምገም ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ድጋፍ ለማድረግና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆን፤ እንዲሁም ከተቋቋመበት ዓለማ አንፃር የአገልግሎት እና የክትትል ድጋፍ በሚያደርግላቸው በናሙና በተመረጡ ቆዳ ማለስለሻና ማልፊያ ፋብሪካዎች ከ 27 ውስጥ 9 (አዋሽ፣ ብሉናይል፣ የኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳርና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካዎች)፣ በጫማ ፋብሪካዎች ከ 23 ውስጥ 8 ( አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ)፣ እና የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ከ 39 ውስጥ 5 ( እንጦቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ችባን ትሬዲንግ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል ቆዳ ውጤቶች) ከ 2008-2010 በጀት ዓመት ከተዘጋጁ የእቅድ አፈፃፀም ከተወሰዱ በድምሩ 22 ፋብሪካዎች እና ባለድርሻ አካል በሆኑ በአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በሁለት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ባህርዳር እና ሞጆ ከተማ አስተዳደርን በማካተት ሲሆን በኦዲቱ የተለዩት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ  በጥራት ላይ የተመሰረተ የግብዓትና ምርት ትስስር እንዲፈጠር በቁም፣ በእርድና ከእርድ በኋላ በቆዳ እንክብከቤ የስልጠና፣ የማማከር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን የማስተባበር ተግባራትን በማከናወን ጥራቱን የጠበቀ ቆዳ በናሙና ለተመረጡ ቆዳ ፋብሪካዎች እንዲደርስ አለማድረጉ፣
- ኢንስቲትዩቱ  ያዘጋጀውን 19 ዓይነት የአገልግሎት ድጋፎችን የያዘ የደንበኞች ቻርተር በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በማሰራጨት የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዲያውቁ አለማድረጉ፣
- ኢንስቲትዩቱ በናሙና ከተመረጡ አምስት የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ፋብሪካዎች(እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ችባን ትሬዲንግ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች) ሲሆኑ፡- ለሶስቱ ለእንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ችባን ትሬዲንግ እና የዚችዓለም መዓዛ የአዋጭነት ጥናት ያልሰራ መሆኑ፣
- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች( አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ባህርዳር እና ሀበሻ) ሲሆኑ፡- ኢንስቲትቱ አነስተኛ ላቦራቶሪ ለማቋቋም የቴክኒካል ስልጠና  ለ 5 ቆዳ ፋብሪካዎች( ባቱ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ፡-
    - ከ8 ጫማ ፋብሪካዎች 4ቱ (ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ እና ሞደርን ዘጌ) ጫማ ፋብሪካዎች  ሁለቱ ኦኬ ጃማይካና ኒው ዊንግ አዲስ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠና ያላገኙ ሲሆን የተቀሩት ሁለቱ ካንጋሮና ሞደርን ዘጌ የቴክኖሎጂ ና የቴክኒክ ስልጠና ያላገኙ ሆኖ ከፍተኛ የሥራ አመራር ስልጠና ያገኙ መሆኑ፣
    - ከ5 የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ፋብሪካዎች 4ቱ (እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች) የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠና ያላገኙ መሆኑ፡፡
    - ከ 9 የቆዳ ፋብሪካዎች 3ቱ(ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና ገላን) ተግባር ተኮር የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ሥልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና የግብዓት ትስስር ድጋፍ መፍጠሩን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ፡-

- ከ8 ጫማ ፋብሪካዎች( አንበሳ፣ጥቁር ዓባይ፣ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) ከአንበሳ ጫማ ፋብሪካ በስተቀር 7ፋብሪካዎችን የትስስሩ ተጠቃሚ ያላደረገ መሆኑ፣
- ከ 5 የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ፋብሪካዎች (እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ችባን ትሬዲንግ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች) ለ 3 ፋብሪካዎች እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ያምሮት ገ/መስቀል እና የዚችዓለም መዓዛ ትስስር እንዲፈጠር ያልሰራ መሆኑ፣
- ከ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች (አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ለአራቱ ብሉናይል፣ ኢትዮጵ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ እና ገላን ቆዳ ፋብሪካዎች ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቆይ እና ለማስተዋወቅ በተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች ለመግባት የሚያስችል የገበያ ልማት እስትራቴጂዎች 4 ጥናቶች ያስጠና ቢሆንም የገበያ ማፈላለግና ትስስር ውጤታማ ባለመሆኑ የኢንስቲትዩቱ ሶስት ተከታታይ (2008- 2010) በጀት ዓመታት የኤክስፖርት የእቅድ-አፈፃፀም ውጤት ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ደረጃ በፕሪሜትር ኮንሰልቲንግ(አማካሪ) ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኩል በሜድባይ ኢትዮጵያ እና በኢንስቲትዩቱ መካከል የኮንትራት ስምምነት በአራት የክፍያ ወቅት በሚፈፀም ክፍያ በጠቅላላው 500,000 የአሜሪካን ዶላር እ.ኤ.አ መጋቢት/2016 የተፈፀመ ሲሆን፤ በፕሮጀክቱ የተያዘው የኤክስፖርት ገቢ በውሉ መሰረት(በጀመሪያ ዓመት 4.75 ሚሊዮን ዩኤስዲ፣ በሁለተኛው ዓመት 45 ሚሊዮን ዩኤስዲ፣ሶስተኛ ዓመት 127.5 ሚሊዮን ዩኤስዲ፣ በአራተኛ ዓመት 229.5 ሚሊዮን እና በአምስተኛ ዓመት 382.25 ሚሊዮን ዩኤስዲ ቢሆንም፤ ከ 2009 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም መረዳት እንደተቻለው በፕሮጀክቱ የተያዘው የኤክስፖርት ገቢ ግብ በእቅድ መሰረት አለመሆኑ የሚል ሲሆን፤ በተገለፀው ሪፖርት ከተመደበው ጠቅላላ በጀት ምን ያህል ክፍያ ተከፍሎ እንደተቋረጠ እና በውሉ ላይ በተገለፀው መሰረት ምን ያህል ገቢ በአሜሪካን ዶላር እንደተገኘ አፈፃፀሙ ያልተገለፀ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ባስጠናው የገበያ እስትራቴጂ ጥናት መሰረት የገበያ ማፈላለግና ትስስር የፈጠረ መሆኑን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች( አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ)

ለአራት ጫማ ፋብሪካዎች ካንጋሮ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ በምርት ናሙና፣ በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የማማከር አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች (አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ)፤ አራት ፋብሪካዎች( ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን እና ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ) የማማከር አገልግሎት ያላገኙ መሆኑ፣
- የምርትና የሰው ኃይል ልማት እና ምርምርን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 8 ፋብሪካዎች (አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) 5 ጫማ ፋብሪካዎች( አንበሳ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ እና ሞደርን ዘጌ) የምርምር ውጤት ድጋፍ ያልደረሳቸው መሆኑ፣
- የምርትና የሰው ኃይል ልማት እና ምርምርን በተመለከተ በቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች በኢንስቲትዩቱ የ2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በተገለፀው መሰረት ሁለት የምርምር ሥራዎች Solar Mobile Leather Case for Cell-Phone charging 50%,and Production of dummy from chrome Shavings 75% የምርምር ሥራዎች ጅምር ክንውኖች የነበሩ ሲሆን በ 2009 በጀት ዓመት ብር 150,000 በጀት ተመድቦላቸው የተቋረጡ መሆኑ፣
- የምርትና የሰው ኃይል ልማት እና ምርምርን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች(አዋሽ፣ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) 6 ቱ ፋብሪካዎች ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን እና ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካዎች ከኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤቶች ድጋፍ ያላገኙ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የዋንኬ እና የአዳል በግ ቆዳዎችን የቆዳ ፋብሪካዎች ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ምርምር በማድረግ በሥራው ለተሰማሩ ወርክሾፕ በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ያደረገ መሆኑን የገለፀ ቢሆንም፤ በናሙና ከተመረጡት 9 የቆዳ ፋብሪካዎች 6ቱ(ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ኮልባ፣ ሞጆ፣ገላን እና ባህርዳር) በወርክሾፑ ያልተሳተፉ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በበዓላትና በአዘቦት ወቅት የእንስሳት እርድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች የጥሬ ቆዳ ግብዓት በእርድ ወቅት ጥንቃቄ እንዲደረግለት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማስተዋወቅ (ፕሮሞሽን) ሥራ ስለመሥራቱ ለመገናኛ ብዙሀን ያቀረባቸውን ማስረጃዎች ያቀረበ ቢሆንም፤ በቆዳ አሰባሰብ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑ፣
- በእርድ ወቅት የቆዳ ጥራት ተጠብቆ ገፈፋ እንዲካሄድ የቆዳና ሌጦ መግፈፊያ ቴክኖሎጂ በቄራዎች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ቴክኖሎጂው ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ ኢንስቲትዩቱ

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በፈፃሚ አካልነት የተመደበ ቢሆንም፤ በኦዲቱ በናሙና በተመረጠው የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት በድርጅቱ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር  ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ በኢንስቲትዩቱ የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩ መገለፁ፣

- የምርት እቅድና ጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ  ኢንስቲትዩቱ ለፋብሪካዎች በስትራቴጂክ እቅድ መሰረት በምርት ማምረት ሂደት እና በጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት ሥራ ለመሥራት የእቅድ ሥራዎች የሚሰራ መሆኑን  ከእቅድ አዘገጃጀትና እቅድ አፈፃፀም (2008- 2010) በጀት ዓመታት ሪፖርት መረዳት የተቻለ ቢሆንም፤ በኦዲቱ በናሙና ለተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች  (አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ)፣ እና  9 ቆዳ ፋብሪካዎች (አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) በምርት ማምረት ሂደት እና በጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት ሥራ ስለመሥራቱ ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የላቦራቶሪ  ፍተሻ ድጋፍ የሰጠ መሆኑን በተመለከተ ለ 6 ጫማ ፋብሪካዎች፡ ለአንበሳ፣ ጥቁ ዓባይ፣  ፒኮክ፣ ኦኬ ጃማይካ ፣ ኒው ዊንግ አዲስ ፣ ፎንታኒ እና ሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የላቦራቶሪ ድጋፍ የሰጠ መሆኑን ሲገልፁ፤ ካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ያላገኘ መሆኑን ሲገለፅ፤ የፍተሻ ድጋፉን ካገኙት ፋብሪካዎች ፒኮክ፣ ኦኬ ጃማይካ እና ሞደርን ዘጌ ኢንስቲትዩቱ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ እየጠየቀ በመሆኑ ድጋፍ እየሰጠ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑን የገለፁ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የማሽን እና ባለሙያ እገዛ ማድረጉን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች 3ቱ (አንበሳ፣ ኦኬ ጃማይካ እና ኒው ዊንግ አዲስ) ጫማ ፋብሪካዎች የተሰጠ ድጋፍ አለመኖሩ፣
- ኢንስቲትዩቱ የለማ ምርት (ኤክስፖርት ስታንዳርድ ዲዛይን) አቅርቦት ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 8 የጫማ ፋብሪካዎች ለሶስት ጫማ ፋብሪካዎች( ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ እና ኒው ዊንግ አዲስ) የምርት ማልማት ሥራ ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የቆዳ ፋብሪካዎች አካባቢን በብክለት ጉዳት ላይ ሳይጥሉ እንዲሰሩ ስልጠና እና ቴክኒካል ድጋፍ የሚሰጥ በመሆኑ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች( አዋሽ፣ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ)  ወደ ውሃ አካላትና ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ የፍሳሽ ደረጃዎችን ጠብቀው የሚለቁ ስለመሆኑ እና የአካባቢ አየር ጥራትን የሚገልፁና ለማይንቀሳቀሱ እና ለሚንቀሳቀሱ የአየር ብክለት ምንጮች የተፈቀዱትን የልቀት መጠኖች የሚወስኑ የአየር ጥራት ደረጃዎችን

ጠብቀው የሚሰሩ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የንፁህ አመራረት ዘዴና የአካባቢ እንክብካቤ መርህን ተከትለው እያመረቱ ስለመሆናቸው በተደረገ አዲት ከ 9ኙ ቆዳ ፋብሪካዎች ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካዎች የሁለተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ኖሯቸው እየሰሩ ሲሆን 7ቱ በአንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ እየሰሩ በመሆናቸው በባካይነት ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች(አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ የኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ለ 7 ፋብሪካዎች  አዋሽ፣  ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኮልባ፣  ሞጆ፣ ገላን እና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካዎች  ስልጠና የሰጣቸው መሆኑ ቢገለፅም በፍሳሽም ሆነ ደረቅ ቆሻሻን ቀላቅሎ በማስወገድ አካባቢ እየበከሉ መሆኑኢንስቲትዩቱ በናሙና ከተመረጡት 9 ቆዳ ፋብሪካዎች 3ቱ (ገላን፣ ኮልባ እና ብሉናይል) የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ያልሰጠ መሆኑ፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ እቅድ፣ የአካባቢ አያያዝ ፕሮፋይል፣ የፍሳሽ ማጣሪያ እና የልቀት ደረጃ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ እንዲሰሩ ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በቆዳው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች በተለያዩ መድረኮች ለሚያነሷቸው ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ላይ የቅንጅታዊ አሰራር ውስንነት የሚታይበት መሆኑ ከ 2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት የተቻለ ቢሆንም፤ ለኢንስቲትቱ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ባለሀብቶች በተለያዩ መድረኮች የሚያነሷቸውን ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት( ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ እንዲሁም ከሌሎች ተቋማት) ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ያለ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት የጋራ እቅድ በማቀድ ሥራዎችን ለመሥራት ጅምር ሥራዎች ያሉ ቢሆንም፤አፈፃፀሙ ክፍተት የሚታይበት መሆኑ በኢንስቲትዩቱ የተገለፀ መሆኑ፣
- በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ጫማ ፋብሪካዎች ጋር የተደረገውን ትብብር በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች 7ቱ (ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣  ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ)  ኢንስቲትዩቱ የምርት ግብዓቶች ተሟልተው እንዲቀርቡ በአቅራቢ እና በአምራች እንዲሁም በአምራች ፋብሪካዎች መካከል የፈጠረው ትብብር/ትስስር የሌለ መሆኑን የገለፁ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የኤክስፖርት የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶችን ምርት ለማሳደግ ከቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት( የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር እና

የቆዳ አቅራቢዎች ማህበር) ጋር በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ልውውጥ ማድረግ የሚያስችለው የዳታ ቤዝ አሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ከቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚደግፍ ተቋም በማስፈለጉ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 41/1991 ተቋቁሟል፡፡ ተቋሙ ለንዑስ ዘርፉ ተለይተው የተሰጡትን 18 ተግባራት በአንድ መስኮት የአገልግሎት ድጋፍ ለመስጠት ይቻል ዘንድ እንደገና ማቋቋም በማስፈለጉ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002 የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ተሻሽሎ ተቋቁሟል፡፡ አገራችን ከድህነት ተላቃ አስተማማኝ የዕድገት ደረጃ ላይ መድረስ የምትችለው የዳበረ ኢንዱስትሪ ሲገነባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪ ልማት ከሌሎች የልማት መስኮች በላቀ ፍጥነት መከናወንና ማደግ እንዳለበት መንግስት ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

2. በዚህ ረገድ መንግስት ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ እና የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህም አንዱ የቆዳ የኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በመላ አገሪቱ የሚገኙ ቆዳና የቆዳ ውጤቶችን እንዲስፋፉ በማድረግ በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪው ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ተጠቃሽ ነው፡፡

3. ሀገራችን ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ በአፍሪካ ቀዳሚና በዓለም ከአስሮቹ ዋና ዋና ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ካላቸው አገሮች አንዷ ብትሆንም ከቆዳና ከቆዳ ውጤቶች የምታገኘው ጥቅም ካላት የእንስሳት ሀብት የሚመጣጠን አይደለም፡፡ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች በዓለም ገበያ ያለው ድርሻም በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቆዳ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ በማድረግ በዓለም ገበያ ያለውን ድርሻ በአሥር እጥፍ ለማሳደግ በየዓመቱ የተለያዩ ግቦችን በማስቀመጥ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ይገኛል፡፡

4. በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዓመት መጨረሻ ከንዑስ ዘርፉ ኤክስፖርት እንዲገኝ የተቀመጠው የ 800 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ግብ አካል የሆነውን የ 2010 በጀት ዓመት 280 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት እቅድ ለማሳካት በተለያየ የአቅም ደረጃ ያሉ የቆዳና የቆዳ ውጤት አምራቾች እንደየምርት ዓይነታቸውና አቅማቸው የበኩላቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

5. ስለሆነም ዘርፉ ለሀገራችን አስፈላጊ በመሆኑ ዘላቂና ፈጣን በሆነ መልኩ ኢንዲስፋፋ በማድረግ በኢንቨስትመንት፣ በምርትና በግብይት ለልማታዊ ባለሀብቱ ቀልጣፋ የቴክኖሎጂ፣ የምክር አገልግሎትና ድጋፍ በመስጠት አገሪቷ ከቆዳ ሀብቷ ከፍተኛ ተጠቃሚ እንድትሆን በተጠናከረ ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ልማት ዘርፉ እየሰራ ይገኛል፡፡

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ራዕይ እና ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር

### ራዕይ

6. ከዘላቂ የአካባቢ ልማት ጋር የተጣጣመ በምርት ብዛትና ስብጥር ረገድ በአፍሪካ ቀዳሚ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪን በመገንባት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 በዓለም አቀፍ ደረጃ የገበያ ድርሻው በ10 እጥፍ ያደገ ኢንዱስትሪን እውን ማድረግ ነው፡፡

### ተልዕኮ

7. የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪን ዘላቂና ፈጣን በሆነ መልኩ ኢንዲስፋፋ በማድረግ በኢንቨስትመንት፣ በምርትና በግብይት ለልማታዊ ባለሀብቱ ቀልጣፋ የቴክኖሎጂ፣ የምክር አገልግሎትና ድጋፍ በመስጠት አገሪቷ ከቆዳ ሀብቷ ከፍተኛ ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ፣

## የኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ

8. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ይሆናል፡፡

### የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር

9. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 181/2002 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-

1. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤

2. በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

3. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት

ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፤

4. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃግብሮችን ማዘጋጀት፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

5. በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤

6. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ዘርፉን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክንኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፣ ለሰልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፤

7. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤

8. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤

9. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፣

   ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታት፣

10. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራት፣በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፤እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ማገዝ፣

11. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዲስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፣

12. ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዲስትሪዎች የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፣

## የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

10. ኢንስቲትዩቱ በመንግስት ስር የሚተዳደር ሲሆን አጠቃላይ ተቋማዊ መዋቅሩን በተመለከተ ዋና ዳይሬክተር እና የየዘርፉ ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች/ የቆዳ ማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የጫማ ማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሲኖሩት፤ በቆዳ ማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ስር 4/አራት ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሲሆን፤ እነርሱም የቆዳ ቴክኖሎጂ፣ኢንቫሮሜንታል፣የምርምርና ፍተሻ እና የትምህርት ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬቶች ናቸው፡፡ በጫማ ማንፋክቸሪንግ/ማምረት/ ዘርፍ 4/አራት/ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሲሆን፤ እነርሱም የጫማ አመራረት ቴክኖሎጂ፣የቆዳ አልባሳትና እቃዎች ማንፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ፣የኢንጅነሪንግ አገልግሎት እና ማርኬቲንግ ዳይሬክቶሬቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዋና ዳይሬክተር ስር ስድስት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች /Supporting staff/ እና ስምንት ዋና የሥራ ሂደቶች/ Line Staff/ አሉ፡፡ የኢንስቲትዩቱ መዋቅር መግለጫ **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

11. ኢንስትቲዩቱ በመዋቅር ደረጃ የተፈቀደለት የሰው ሃይል ብዛት 427 ሲሆን፤ አሁን በሥራ ላይ ያለው የሰው ሃይል ብዛት 314 ሆኖ፣ቀሪው 113 የሚሆን ቦታ በሰው ሃይል ሳይሸፈን እስከ ሚያዚያ 25/ 2010 ዓ.ም ይገኛል፡፡

### የፋይናንስ ምንጭ

12. ኢንስቲትዩቱ ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት ሲሆን ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ አመት ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | | ሥራ ላይ የዋለ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመብለጥ | በማነስ | |
| 2008 | 110,756,570.00 | 102,804,441.30 | - | 7,952,128.70 | 93% |
| 2009 | 100,270,199.61 | 90,772,458.17 | - | 9,497,741.44 | 91% |
| 2010(እስከ መጋቢት 30) | 112,819,480.00 | 81,406,950.12 | - | 31,412,529.88 | 72.2% |

## የኢንስቲትዩቱ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DISCRIPTION)

**የጫማና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ**

**የጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት**

- የኢንዱስትሪ ፋላጎት ጥያቄ ለኢንስቲትዩት የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡
- የስልጠና ፋላጎት ለኢንስቲትዩት ያቀርባል፡፡
- በኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ አመራር ለትምህርትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ለአፈጻጸም ይመራል፡፡
- ለትምህርትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ባለሙያ እንዲመደብ ለጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት በውስጥ ማስታወሻ ጥያቄ ያቀርባል፡፡
- ዳይሬክቶሬቱ ባለሙያ በመመደብ ስልጠናውን ይሰጣል፡፡
- በትምህርትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የፋብሪካው ግብረ-መልስ ተሰብስቦ፣ ተደራጅቶና የእርካታ ደረጃ ለዳይሬክቶሬቱ ይላካል፡፡ ይህ የሥራ ፍሰት ዑደቱን ጠብቆ በቀጣይነት የሚከናወን ሥራ ነው፡፡

**የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ጓንት ኢንዱስትሪ ልማት**

- ፋብሪካዎች የቴክኒክ ድጋፍ ጥያቄን በደብዳቤ ያቀርባሉ፡፡
- ደብዳቤው ከኢንስቲትዩቱ መዝገብ ቤት በቀጥታ ወደ ሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ይመራል፡፡
- ዳይሬክተሩም ወደ ሞዴል ፋብሪካ ቡድን ኮፒ አድርጎ ይመራል፡፡
- ሞዴል ፋብሪካ ቡድንም የተፈለገውን የቴክኒክ ድጋፍ ከሰጠ በኋላ ባለው የዋጋ ተመን መሰረት ዋጋ ስሌት በማዘጋጀት ለፋይናንስ ክፍያ እንዲፈፅም ይልከዋል፡፡
- ፋብሪካው የተዘጋጀውን የክፍያ መጠን በመያዝ ክፍያውን ይፈፅምና ንብረቱን ይዞ ለመውጣት የመውጫ ፎርሙን ሞዴል ፋብሪካና ዳይሬክተሩ እንዲፈርም በማድረግ ንብረቱን ይዞ ይመለሳል፡፡

### የክዋኔ ኦዲቱ ዓለማ፡-

13. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 181/2002 በአንቀጽ 5 ዓለማ ስር ኢንስቲትዩቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዲስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት እንዳለበት የተመለከተ በመሆኑ ይህንንም ተግባር ለመወጣት በማቋቋሚያ ደንቡ ላይ የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባር የተገበረ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ድጋፍ ለማድረግና በኢንስቲትዩቱ አሰራርም ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

14. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ(Potential Audit Area) የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር ላይ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አፈፃፀም ማከናወኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

## የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡-

15. በተመረጠው የኦዲት አካባቢ(Potential Audit Area) አራት(4) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና አንድ ንዑስ ትኩረት አቅጣጫ ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ኢንስቲትዩቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎችን ለማሳደግ፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የአሰራር ስርዓቶችን የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
2. ኢንስቲትቱ የቆዳ ማንፋክቸሪንግ ልማትን ለማጠናከር የሚያግዙ የጥናትና ምርምር፣ የአቅም ግንባታ፣ የግብዓት፣ የገበያ ማስተዋወቅና ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የድጋፍ እና ክትትል አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣
3. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ አሟልተው ስለማምረታቸው የሚያረጋግጥ መሆኑን መገምገም፣

3.1. ኢንስቲትዩቱ ቆዳና የቆዳ ውጤቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በማምረት ሂደት ውስጥ የአካባቢ ጥበቃን አዋጅ መሰረት በማድረግ በህብረተሰቡ እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ ሳያደርጉ የሚያመርቱ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ መሆኑን መገምገም፣

4. ኢንስቲትዩቱ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሀገሪቷ ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ወደምታገኝበት ደረጃ እንድትደርስ እና ወደ ውጭ የሚላክ የምርት መጠን እንዲያድግ ከፋብሪካዎች ባለንብረቶች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን መገምገም፣

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁባቸው ማስረጃዎች

16. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት አራት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና አንድ ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫን ለመመዘን የሚረዱ 33 የመመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፤ የኦዲት መስፈርቱን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ማስረጃዎች በአባሪ 4 የተያያዘ ሲሆን፤ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው

አስተያየታቸውን የሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-

### የኦዲቱ ወሰን

17. የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ 2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር ሥራዎች አፈፃፀም ቀልጣፋነትንና ውጤታማነትን ግምገማ በተመለከተ ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆን፤እንዲሁም ከተቋቋመበት ዓለማ አንፃር የአገልግሎት እና የክትትል ድጋፍ በሚያደርግላቸው በናሙና በተመረጡ ቆዳ ማለስለሻና ማልፊያ ፋብሪካዎች ከ 27 ውስጥ 9ኙ /33.3%/(አዋሽ፣ ብሉናይል፣ የኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳርና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካዎች)፣ ጫማ ፋብሪካዎች ከ 23 ውስጥ 8ቱ /34.8%/( አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘኔ) እና የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ከ 39 ውስጥ 5ቱ /12.8%/( እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ችባን ትሬዲንግ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል ቆዳ ውጤቶች ከ 2008-2010 በጀት ዓመት የውጭ ኤክስፖርት ገቢ እቅድ አፈፃፀማቸው እየቀነሰ መሄድን በተመለከተ በናሙና መምረጫ መመዘኛ በመምረጥ በድምሩ 22 ፋብሪካዎች እና ባለድርሻ አካል የሆኑ አዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት፣ ግብርና ሚኒስቴር እና ሁለት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ባህርዳር እና ሞጆ ከተማ አስተዳደር እንዲካተቱ በማድረግ በኦዲቱ ተሸፍነዋል፡፡(የናሙና መመዘኛ መምረጫ በአባሪ 3 ተያይዟል)

### የኦዲቱ ዘዴ

18. በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና ኢንስቲትዩቱ የአገልግሎት እና ክትትል ድጋፍ በሚሰጣቸው የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች በመገኘት አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፤ የመስክ ምልከታ በማድረግ እና መረጃዎችን በመተንተንና በማነፃፀር/Analysis/ ማካሄድ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

## ኢንስቲትዩቱ ወቅታዊ መረጃና ግንዛቤ መስጠቱን በተመለከተ

19. ኢንስቲትዩቱ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማታዊ ባለሀብት እና ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ጋር መንግስት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎች እና ተግባሮች ላይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

20. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የሰራ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-ለኢንስቲትቱ የሥራ ኃላፊዎች/ማኔጅመንት/ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚገናኝበትና መረጃ የሚለዋወጥበት የአሰራር ስርዓት ያለው መሆኑን እና ይህም ከንዑስ ዘርፉ (የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች ባለሀብቶች) እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት(ገቢዎችና ጉምሩክ፣ ባንክ፣ መብራት ኃይል ወ.ዘ.ተ) በ 3 ወር አንድ ጊዜ በሚዘጋጀው በህዝብ ክንፍ መድረክ፣ ከህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የኢንዱስትሪ ቋሚ ኮሚቴ በ 3ወር አንድ ጊዜ፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የበላይ አመራር ጋር በየወሩ፤ እንዲሁም ከጠቅላይ ሚኒስቴር ብሄራዊ የኤክስፖርት ካውንስል ጋር በየሁለት ወሩ መረጃ የመለዋወጥ ስርዓት ያለው ሆኖ በእነዚህ መድረኮች የንዑስ ዘርፉን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ አሰራሮች ላይ ውይይት የሚያደረግ ሲሆን፤አላሰራ ያሉ መመሪዎችና ደንቦች እንዲሻሻሉ ተደርጎ የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት የሚያደረግ ቢሆንም አፈፃፀሙ ሲታይ በየዓመቱ እየቀነሰ መሄዱ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩት ሥራዎች በሚፈለገው ልክ እንዳልሆኑ በየጊዜው ከሚደረጉ የጋራ መድረኮች ማረጋገጥ መቻሉን ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

21. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ኢንስቲትዩቱ በሰጠው መልስ በንዑስ ዘርፍ ደረጃ ከተለያዩ የመንግስት ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ቀጣይነት ያለው ጥረት እየተደረገ ቢሆንም፤ አሁንም በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልተደረሰ መሆኑ ተገልጿል፡፡

22. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት በቆዳ ንዑስ ዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎችን፣ ደንቦች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎች እንዲሁም አዋጆች ላይ ግንዛቤ መፍጠሩን በተመለከተ የተለያዩ ደብዳቤዎችን በማቅረብ ውይይት መደረጉን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም በኦዲት ሂደት እና በነባራዊ

ሁኔታ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ በተሰጡት መልሶች የተሰሩት ሥራዎች በሚፈለገው ልክ እንዳልሆኑ በየጊዜው ከሚደረጉ የጋራ መድረኮች ማረጋገጥ መቻሉን የገለፀ በመሆኑ ውጤታማ ሥራ ያልተሰራ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በኦዲት ሂደት ወቅት እና በነባራዊ ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ ከተሰጡ መልሶች ተገንዝቧል፡፡

23. ኢንስቲትዩቱ አሳሰራ ያሉ መመሪያዎችና ደንቦች ላይ ያሉ ችግሮችን የሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ ግንዛቤ ኖሯቸው በየሥራ ድርሻቸው የማስተካከል ሥራ እንዲሰሩ ጥረት ማድረጉ ኃላፊነት መወጣቱን የሚያመለክት ቢሆንም፤ ችግሮችን ከማስተካከል አኳያ በየደረጃው ተሳትፎ ከሚያደረጉ ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩ ሥራዎች በተፈለገው ሁኔታ ውጤታማ አለመሆናቸው በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ኤክስፖርት በሚገኘው ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲኖር አስተዋፆ ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የሚሰጣቸውን የድጋፍ አገልግሎቶች ማሳወቁን በተመከተ

24. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን የድጋፍ አገልግሎቶች በግልፅ ሊያሳውቅና አገልግሎቱን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
25. ይሁን እንጅ ኢንስቲትዩቱ በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- ኢንስቲትዩቱ የሚሰጣቸውን የድጋፍ አገልግሎቶች በቆዳ ኢንዱስትሪ ለተሰማራው ልማታዊ ባለሀብት በግልፅ የማሳውቅና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የማድረግ ችግር የታየበት መሆኑ ከ 2008 በጀት ዓመት የ 12 ወራት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡
26. ስለሁኔታው በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች/ማኔጅመንት/ በጋራ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በ 2007 ዓ.ም ኢንስቲትዩቱ የደንበኞች ቻርተር አዘጋጅቶ ወደ ተግባር የገባ ቢሆንም፤ የአገልግሎቱ ዓይነትና የሚያስፈልጉ ቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች በአብዛኛው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ክፍሎች ግልፅ በሆነ ቦታ ያልተለጠፈ በመሆኑ ድጋፍ ፈላጊዎች በሚፈለገው ልክ እንዲረዱ ያለማድረግ ችግር የነበረ መሆኑን ገልጸዋል፡
27. ኢንስቲትዩቱ ያዘጋጀውን 19 ዓይነት የአገልግሎት ድጋፎችን የያዘ የደንበኞች ቻርተር በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ያለማሰራጨቱ እና ስለሁኔታውም እንዲያውቁ በግልፅ ቦታ አለመለጠፉ አገልግሎት ፈላጊዎች የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ በየዓመቱ በእቅድ ተይዘው የሚሰሩ ሥራዎች አፈፃፀም ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት ድጋፍ ማድረጉን  በተመለከተ

28. ኢንስቲትዩቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
29. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የጫማ ፋብሪካን በሚመለከት በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡት 8 ፋብሪካዎች( አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) የአዋጭነት ጥናት የተዘጋጀላቸው ስለመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ ለጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ ጫማ ፋብሪካዎች ነባር በመሆናቸው ድጋፍ እንዳልተደረገላቸው ገልፀው ነገርግን ለአንበሳ ጫማ ፋብሪካ ማስፋፊያ የተጠና የማስፋፊያ የአዋጭነት ጥናት በኢንስቲትዩቱ መገምገሙን አሳውቀው በአሁኑ ወቅት አዲስ ለተቋቋሙት ለኢትዮ ኢንተርናሽናል ፉትዌር ክላስተር፣አሊቤርቴ ሊሚትድ እና ለቦስቴክስ ኃላ/የተ/የግ/ማ ለመሳሰሉት ጥናት ማጥናታቸውን የጥናቶች መጠየቂያና መረከቢያ ደብዳቤዎች በማስረጃነት በማቅረብ  ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
30. የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ጫማ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የአንበሳጫማ ፋብሪካ ማስፋፊያን በሚመለከት የአንበሳ ጫማ ፋብሪካ ሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ እና የሽያጭ ማስፋፊያ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንስቲትዩቱ የተጠና የማስፋፊያ የአዋጭነት ጥናት የገመገመላቸው መሆኑን ሲገልፁ የተቀሩት 7 ፋብሪካዎች የሥራ ኃላፊዎች ፋብሪካዎቻቸው ነባር መሆናቸውን በመግልፅ የአዋጭነት ጥናት ያላስፈለጋቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡
31. የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎችን በተመለከተ በናሙና የተመረጡት አምስት( እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ችባን ትሬዲንግ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል ቆዳ ውጤቶች) ሲሆኑ፡-  በኢንስቲትዩቱ ቆዳ አልባሳት እና እቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የኒቨርሳል ቆዳ አልባሳት ፋብሪካ ነባር በመሆኑ የአዋጭነት ጥናት ያልተሰራለት ሲሆን፤ ለያምሮት ገ/መስቀል(ሮዛ አቢሲኒካ) የአዋጭነት ጥናት የተሰራ ሆኖ ለተቀሩት ሶስቱ ለእንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ችባን ትሬዲንግ እና የዚችዓለም መዓዛ የአዋጭነት ጥናት በኢንስቲትዩቱ አለመሰራቱን አሳውቀዋል፡፡
32. ኢንስቲትዩቱ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በቀረበለት ወቅት የአዋጭነት ጥናትን በተመለከተ በኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት መልስ የአዋጭነት ጥናት ኢንስቲትዩቱ የሚያጠናው ጥያቄ ሲቀርብለት ብቻ መሆኑን

የገለፁ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ከሚሰጣቸው ድጋፎች ባዘጋጀው የደንበኞች ቻርተር ላይ የአዋጭነት ጥናት ማዘጋጀት አንዱ በመሆኑ የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡

33. ኢንስቲትዩቱ ረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት ለቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካዎች የሚጠና የአዋጭነት ጥናትን በተመለከተ በሰጠው መልስ የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት በኩል ኢንስቲትዩቱ ብቸኛ አማራጭ ባለመሆኑ እንደ ባለሀብቱ ፍላጎት በሥራው ላይ ፍቃድ ያላቸውን የግል አማካሪ ግለሰቦችና ድርጅቶች በመጠቀም እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ የሚችሉ መሆኑን በመግለፅ ከዚህ አንፃር የዚች ዓለም መዓዛ፣ እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብና ችባን ትሬዲንግ ሥራውን በሌሎች አካላት ሊያሰሩ የሚችሉበት አግባብ ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቱን ለማግኘት ጥያቄ ያቀረቡበት ሁኔታ ባለመፈጠሩ የድጋፍ አገልግሎቱን ለመስጠት በኢንስቲትዩቱ በኩል የሚያነሳሳ ምንም ምክንያት እንዳልነበረ ተገልጿል፡፡

34. በኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ተግባር ላይ እንደተመለከተው በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች አመራረት ሂደት ባሉ መስኮች በሚደረጉ የአዋጭነት ጥናቶች ከፕሮጀክት ኢንጅነሪንግ ዳሬክቶሬት ጋር በመተባበር የሚሰራ መሆኑ እና በኢንስቲትዩቱ በተዘጋጀው የተገልጋዮች ቻርተር ላይም የፕሮጀክት ፕሮፋል እና የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት የአገልግሎት ድጋፍ  መስጠት እንዳለበት ተገልጿል፡፡

35. እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ በመሆኑ ፋብሪካዎቹ ድጋፍ አላገኘንም እያሉ በገለፁበት ሁኔታ ጥያቄ አልቀረበልንም ወይም በሌላ አሰርተው ሊሆን ይችላል የሚለውን የኦዲት ቡድኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

36. ኢንስቲትዩቱ በሥራ ተግባሩ እና ባዘጋጀው የተገልጋዮች ቻርተር ላይ የተመለከቱ አገልግሎቶችን ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊዎች በቅርብ በመገኘት ድጋፍ ካልሰጠ በኢንቨስትመንት ማስፋፋት ሂደት ሊገኝ የታሰበው ግብ እንዳይሳካ እና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በቆዳና ቆዳ ውጤቶችዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ መደገፉን በተመለከተ

37. ኢንስቲትዩቱ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ የቴክኒካል ስልጠናና ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ 5ቱ ፋብሪካዎች ማለትም(ባቱ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ)አነስተኛ ላቦራቶሪ ለማቋቋም ከኢንስቲትዩቱ የቴክኒካል ስልጠናና ድጋፍ ያላገኙ

መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አዋሽ የቆዳ ፋብሪካ ግን ከኢንስቲትዩቱ የተለያየ ድጋፍ ማግኘቱን ሲገልፅ፣ ብሉናይል የቆዳ ፋብሪካ የማምረት ሥራ ያቆመ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና የሞጆ ቆዳ ፋብሪካዎች ቀደም ሲል ላቦራቶሪ ያላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

39. የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የቴክኒካል ድጋፍ ለማድረግ የፋብሪካዎች ዝግጁነት፡- በሰው ሃይል፣ በመሳሪያ፣ በኬሚካልና በመሥሪያ ቦታ፣ የውሃና የኤሌክትሪክ ዝርጋታ እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ማሟላታቸውን ሲገልፁ የሚደረግ ድጋፍ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

40. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ይሄን ቢሉም ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው የተገልጋዮች ቻርተር ላይ እንደተመለከተው ከሚሰጣቸው ድጋፎች አንዱ የቆዳ ፋብሪካዎች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ ቴክኒካል ድጋፍ መሰጠት መሆኑ በመገለፁ እና በዚህ ጉዳይ የተደረገው ድጋፍ ዝቅተኛ በመሆኑ ወደ ኢንስቲትዩቱ ቀርበው ድጋፍ ካልጠየቁ ተብሎ የተሰጠውን መልስ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

41. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት በሰጠው መልስ ከላይ ለነበራዊ ሁኔታ የሰጠውን መልስ በድጋሚ የገለፀ ሆኖ በኦዲቱ በስም ከተጠቀሱት 5ቱ( ባቱ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳርና ሀበሻ) የቆዳ ፋብሪካዎች መካከል 2ቱ(ሞጆና ገላን) የቆዳ ፋብሪካዎች የተጠቀሰውን የድጋፍ አገልግሎት ለማግኘት ጥያቄ ያቀረቡበት ሁኔታ የሌለ ሲሆን፤ የተቀሩት 3ቱ( ባቱ፣ ባህርዳርና ሀበሻ) የቆዳ ፋብሪካዎችን በተመለከተ ግን ድጋፉን ለመስጠት በተደረገ ጥረት ማሟላት የሚገባቸውን የመሳሪያዎች ዝርዝርና እስፔስፊኬሽን እንዲሁም የኬሚካል ዝርዝር የተሰጠ ቢሆንም በወቅቱ የተጠቀሱትን ግብዓቶች በማሟላት ለቀጣይ የቴክኒክና የባለሙያ ድጋፍ ጥያቄ ያላቀረቡ በመሆኑ የድጋፍ አገልግሎቱን ማከናወን አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

42. ሆኖም በረቂቅ ሪፖርቱ ሞጆና ገላን ፋብሪካዎች ጥያቄ ያላቀረቡ መሆናቸው የተገለፀ ሲሆን ለቀሩት ባቱ፣ ባህርዳርና ሀበሻ ድጋፍ ለመስጠት ኢንስቲትዩቱ ጥረት ያደረገና ለቀጣይነትም በፋብሪካዎቹ ጥያቄ አለማቅረብ ምክንያት ያልተሳካ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም የተደረገው ድጋፍ በማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፤

43. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ ተገቢውን የቴክኒካል ስልጠናና ድጋፍ አለማድረጉ ኢንዱስትሪዎቹ ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንዳያመረቱ እና የአካባቢ ብክለትን ባግባቡ እንዳይከላከሉ ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠናን መስጠቱን በተመለከተ

44. ኢንስቲትዩቱ የጫማ ፣የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች፣እንዲሁም የቆዳ ማለስለሻ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የሥራ አመራር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ሊያዘጋጅ እና ሊሰጥ ይገባል፡፡
45. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች ውስጥ 4ቱ ማለትም (ኦኬ ጀማይካ ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ካንጋሮ እና ሞደርን ዘጌ) ጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ በምርት አመራረት፣ በጥራት፣ በፋሽን ዲዛይን (ቴክኖሎጂ)፣ ጥገና ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠና ድጋፍ ያልሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም አንበሳ ጫማ ፋብሪካ ስልጠናውን መውሰዱን ቢገልፅም፣ የሚሰጠው ስልጠና ከፋብሪካዎች የሙያ ብቃት ደረጃ ጋር የሚመጣጠን ተግባርን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ክፍተት የሚታይበት መሆኑን ሲገልፅ 3ቱ (ፒኮክ፣ ጥቁር ዓባይ እና ፎንታኒና) ጫማ ፋብሪካዎች ስልጠና ያገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
46. ስለሁኔታው ለጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢንስቲትቱ በ 2008 በጀት ዓመት የፋብሪካዎችን የማምረት አቅም እና በአፈፃፀም ላይ ያሉ ችግሮችን በማየት በአዲስ አበባ በሚገኙ ሰባት የቆዳ እና ጫማ ፋብሪካዎች ላይ ደሰሳ ጥናት አድርጎ በወቅቱ በተነሱ ሀሳቦች እና በጋራ በሚከናወኑ ተግባሮች ላይ ከእያንዳንዱ ፋብሪካ አንፃር እንዲለዩ የተደረጉ መሆኑን ቢገልጹም በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት ተግባር ተኮር ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ ሲሆን ኦዲቱ በተከናወነበት በ 2010 በጀት ዓመት ከላይ ስማቸው የተገለፁት 5 ፋብሪካዎች ተገቢውን ተግባር ተኮር የስልጠና ድጋፍ ያላገኙ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ለየፋብሪካወቹ የሥራ ኃላፊዎች ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡
47. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ለጫማ ፣ለቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች፣እንዲሁም ለቆዳ ማለስለሻ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ልማት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የሥራ አመራር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ሊያዘጋጅ እና ሊሰጥ ይገባል፡፡
48. ኢንስቲትዩቱ የነበራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት የአመራር ክህሎት የሰለጠኑ ሰራተኞች ከሞጆ ቆዳ ፋብሪካ 1፣ ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ 2፣ ከባቱ ቆዳ ፋብሪካ 1 እና ከአንበሳና ከፎንታኒና ጫማ ፋብሪካዎች ከእያንዳንዳቸው 1 ስም ዝርዝር የያዘ የስልጠና መከታተያ ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም የቴክኖሎጂ እና የቴክኒክ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን መሰጠታቸውን የሚያመለክት ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡
49. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት 4ቱ (ኦኬ ጀማይካ ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ካንጋሮ እና ሞደርን ዘጌ) ጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ በምርት አመራረት፣ በጥራት፣

በፋሽን ዲዛይን (ቴክኖሎጂ)፣ ጥገና ፣ የቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠና ድጋፍ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ባቀረበው ማስረጃ የፕሮጀክት አስተዳደር ስልጠና እ.ኤ.አ መስከረም 18- 22/2017 ከሰው ሀብት ክፍል ከኦኬ ጃማይካ ስልጠና የወሰደ የአንድ ግለሰብ ስም ከመቆጣጠሪያ( አቴንዳንስ) መመልከት የተቻለ ሲሆን የከፍተኛ አመራር ክህሎት ስልጠናን በተመለከተ ካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ( 19/12/08፣ 21/12/08 እና 22/12/2008 ዓ.ም)፣ ሞደርን ዘጌ 05/01/09፣ 06/01/09 እና 08/01/2009 ዓ.ም) የወሰዱ ስለመሆኑ የስልጠና መቆጣጠሪያ ( አቴንዳንስ) ታይቷል፡፡ይሁን እንጂ ፋብሪካዎቹ የቴክኖሎጂ እና የቴክኒክ ተግባር ተኮር ስልጠናዎች ስለመውሰዳቸው የሚያመለክት ማስረጃ አልቀረበም፡፡

50. በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 5 የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ ሊሰጥ ከሚገባቸው የቴክኖሎጂ፣ ቴክኒክ እና የሥራ አመራር ስልጠና ድጋፍ፤ የቴክኒክ ስልጠና ድጋፍ ለቺባን ትሬዲንግ ፋብሪካ ብቻ የሰጠ ሲሆን፤ለእንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል ቆዳ ውጤቶች ያልሰጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብና ዩኒቨርሳል የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ የፓተርን ሥራና ዲዛይን(ቴክኖሎጂ) ከየካቲት 13- 27/2009 ዓ.ም ስልጠና እንዲወስዱ የተደረገ መሆኑን ሲገልፁ ሌሎቹ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ችባን ትሬዲንግ ፋብሪካዎች ስልጠና የወሰዱ ስለመሆናቸው መልስ ያልሰጡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

52. የረቂቅ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት ኢንስቲትዩቱ እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች የፓተርን ሥራና ዲዛይን ስልጠና(ቴክኖሎጂ) ከእ.ኤ.አ 20/02/2017 — 03/03/2017 ስለመውሰዳቸው የሚያመለክት ማስረጃ ያቀረቡ ሲሆን ለሌሎቹ 3ቱ የቀረበ ማስረጃ የሌለ ሲሆን የቴክኒክ እና የአመራር ክህሎት ስልጠና ስለመሰጠቱ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን የኦዲት ቡድኑ ይገልፃል፡፡

53. በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 የቆዳ ፋብሪካዎች የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር ፕሮጀክት ኳሊቲ እና ኢንቫሮመንት ማናጀር በቂ ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑን ሲገልፁ ብሉናይል እና የገላን ቆዳ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጆች፤ ፋብሪካዎቹ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የሥራ አመራር ተግባር ተኮር ሥልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡ሆኖም የተቀሩት 6ቱ ፋብሪካዎች የሥራ ኃላፊዎች ስልጠና መሰጠቱን አሳውቀዋል፡፡

54. ስለሁኔታው ስልጠናውን ያልወሰዱ 3 ፋብሪካዎችን በተመለከተ በኢንስቲትዩቱ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በቆዳ ቴክኖሎጂ የንድፈ ሀሳብ እና ተግባር ስልጠና ለኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና ለሞጆ ቆዳ የተሰጡ ስልጠናዎችን አቴንዳንስ እና ሰርተፊኬቶች እንደ ማስረጃነት ማየት የሚቻል መሆኑን ሲገልፁ ብሉናይል እና ገላን የቆዳ ፋብሪካዎችን በተመለከተ መልስ ያልሰጡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

55. የኦዲት ቡድኑ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ለኢንስቲትዩቱ ባቀረበበት ወቅት በኢንስቲትዩቱ የተሰጠ መልስ ከፍተኛ የአመራር ክህሎት አቅም ግንባታ እና ዓለም አቀፍ የቢዝነስ እስትራቴጂ ስልጠና ገላን ቆዳ ፋብሪካ የወሰደ መሆኑ ተገልፆ በማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ እና በምርት ሂደት ቁጥጥር ስልጠናዎች ላይ እንዲሳተፍ ጥሪ ቢደረግለትም ያልተገኘ ስለመሆኑ በኢንስቲትዩቱ የተገለፀ ቢሆንም ለስልጠናውም ሆነ ለተደረገው ስልጠና ጥሪ የቀረቡ ደጋፊ ማስረጃዎች ያልቀረቡ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበለውም፡፡

56. የረቂቅ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት ኢንስቲትዩቱ በሰጠው መልስ ብሉናይል ፋብሪካ በመንገድ ምክንያት በተጠቀሱት ዓመታት የምርት ሥራ ማቆሙን ገልፀው ገላን ፋብሪካ በራሱ ምክንያት የስልጠና ድጋፍ አለማግኘቱን ገልጿል፡፡

57. በኢንስቲትዩቱ ከላይ የተገለፁት መልሶች የተሰጡ ቢሆንም፤ ብሉናይል ፋብሪካ የስልጠና ድጋፍ ስለማግኘቱ በኦዲት ቡድኑ የቀረበለት ጥያቄ ሥራ ይሰራ የነበረበት ወቅትን መሰረት አድርጎ በመሆኑ እና ለዚህም ፋብሪካው የሰጠው መልስ የስልጠና ድጋፍ ያላገኘ መሆኑን ሲሆን፤ የገላን ቆዳ ፋብሪካን በተመለከተ ፋብሪካው ድጋፍ አላገኘሁም ብሎ መልስ በሰጠበት ሁኔታ ኢኒስቲትዩቱ ምክንያቱን በማስረጃ ሳያስደገፍ በራሱ ችግር የስልጠና ድጋፍ አላገኘም በማለት የሰጠው መልስ አግባብነት የሌለው መሆኑ በኦዲት ቡድኑ ታምኖበታል፡፡

58. ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው የተገልጋዮች ቻርተር ውስጥ የቴክኖሎጂ መረጣ እና የጥገናና ቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ መስጠት፤ እንዲሁም ትምህርትና ስልጠና አዘጋጅቶ መስጠት የሚሉ የተመለከቱ ሲሆኑ፤ በተጨማሪም በጫማ፣ በቆዳ አልባሳት እና እቃዎች እና ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬቶሬት ተግባራት ላይ የቆዳ አመራረት ቴክኖሎጂን የቴክኒክ እና የጥራት እና አካባቢያዊ ሥራ አመራር ድጋፍ አገልግሎት መስጠት የሚሉ የተቀመጡ በመሆናቸው፤ ከፋብሪካዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ተግባር ተኮር ስልጠናዎች በመስጠት ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የማይተገበሩ ከሆኑ በፋብሪካዎቹ እና በኢንስቲትቱ መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት የሚያራርቁ ከማድረግም በላይ ኢንዱስትሪዎቹ የሚያመርቷቸው ምርቶች በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ትስስር መፍጠርን በተመለከተ

59. ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና የግብዓት ትስስር ድጋፍ ሊፈጥር ይገባል፡፡

60. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች (አንበሳ፣ጥቁር ዓባይ፣ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጀማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) ሲሆኑ፡- 1. ጥቁር ዓባይ 2.ፒኮክ 3.ካንጋሮ 4. ኦኬ ጀማይካ 5. ኒው ዊንግ አዲስ 6. ፎንታኒና እና 7. ሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎት በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና ግብዓት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያላደረገ መሆኑን የፋብሪካዎቹ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ሲገልፁ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ ብቻ የትስስሩ ተጠቃሚ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

61. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ጥሬ ቆዳና ሌጦን በተመለከተ አቅራቢዎች በተለይ በበዓላት ወቅት በመጋዘናቸው ክምችት በሚፈጠር ጊዜ ትብብር እንዲደረግላቸው በየጊዜው ጥያቄ የሚያቀርቡ በመሆኑ ይህን መነሻ በማድረግ የቆዳ ፋብሪካዎችን በስልክ እና በአካል በመገኘት የማግባባት ሥራ በመሥራት የጥሬ ቆዳ ግብዓቱን እንዲገዙና ትስስር እንዲፈጥሩ የተደረገ መሆኑን ሲገልፁ፤ ለማሳያነት የኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር ከአንበሳ፣ ከራምሴ እና ከፒታርድ ፕሮዳክትስ ጋር ባለቀለት ቆዳ ትስስር እንዲፈጥሩ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

62. የሥራ ኃላፊው በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች ለአንዱ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ ብቻ የምርትና የግብዓት ትስስር የተፈጠረ ስለመሆኑ በኦዲቱ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

63. በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 5 የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ፋብሪካዎች በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ 3ቱ (እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ፣ ያምሮት ገ/መስቀል እና የዚችዓለም መዓዛ) ኢንስቲትዩቱ የምርትና የግብዓት ትስስር በፋብሪካዎች መካከል እንዲፈጠር ያልሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

64. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በስም ከተጠቀሱት አምስት ፋብሪካዎች ውስጥ ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ የራሱ የሆነ ቆዳ አቅራቢ እህት ድርጅት አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ያለው ሲሆን፤ ከቀሪ አራት ፋብሪካዎች ውስጥ በ 2010 ዓ.ም ቺባን ትሬዲንግ ከባቱ ጋር ትስስር በመፍጠር ቆዳ እንዲረከብ በደብዳቤ የተገለፀ ሲሆን፤ እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ቆዳ እንዲረከብ የተደረገ ሆኖ አለመግባባት ቢፈጠርም፤ችግሩ እንዲፈታ የተደረገ መሆኑን ገልፀው ለማሳያነት ባቱ የቆዳ ማልፊያ ፋብሪካ

ለችባን ትሬዲንግ የፃፈው ደብዳቤ እና እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የፃፈውን የቅሬታ ደብዳቤ በማስረጃነት ያያዙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

65. ኃላፊው በእንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ እና አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ መካከል የተፈጠረ ቅሬታ መፍትሄ ማግኘቱን የገለፁ ቢሆንም እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ ትስስር ያልፈጠረ መሆኑን የገለፀ ሲሆን፤ ያምሮት ገ/መስቀልንና የዚችዓለም መዓዛን በተመለከተ መልስ ያልሰጡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

66. በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ 4ቱ (ብሉናይል፣ ኢትዮጵ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ እና ገላን) ቆዳ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያላደረገ መሆኑን ሲገልፁ የተቀሩት 5ቱ (አዋሽ፣ባቱ፣ ሞጆ፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ትስስር የፈጠሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

67. ስለሁኔታው ትስስሩ ያልተፈጠረላቸውን 4 ቆዳ ፋብሪካዎችን በተመለከተ በኢንስቲትዩቱ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የቆዳ ፋብሪካዎች በግብዓትና ምርት ትስስር እንዲፈጥሩ በተደረገ ክትትልና ድጋፍ በከፊል የለፋ ቆዳ ቅብብሎሽ እንዲኖር መደረጉን እና በተያያዘም ያለቀለት ቆዳ ለቆዳ ውጤቶች አምራቾች እንዲቀርቡ የተደረገ መሆኑን ቢገልፁም፤ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

68. እንዲሁም በአዲስ ከተማ መስተዳድር በሚገኙ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች መጋዘኖች የሚገኘውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ክምችት በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት እና ከኢትዮጵያ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ማህበር ጋር የሰራውን የመስክ ምልከታ ጥናት ሥራ መስከረም 2010 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት የቴክኒክ ቡድኑ በተወሰኑት 12 የጥሬ ቆዳና ሌጦ መጋዘኖች ውስጥ 195,000 የበግ ሌጦ፣ 58,200 የፍየል ሌጦ፣ 80,000 የዳልጋ ከብት ቆዳ፣ 150,000 የበግ ፒክልድ ቆዳ እና 50,000 የፍየል ዌት ብሉ ቆዳ በድምሩ 533,200 ለቆዳ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን በከፊል የለፋና የጥሬ ቆዳ ሌጦ ምርት ተከማችቶ የተገኘ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ በወቅቱ የሚረከብ የቆዳ ፋብሪካ ባለመገኘቱ የጥራት ደረጃው የቀነሰ/የተበላሸ 91,800 የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ክምችት የተገኘ መሆኑ ከመስክ ምልከታ ጥናት የቀረበ ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡

69. በኢንስቲትዩቱ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በቀረበበት ወቅት የተበላሸ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ክምችትን በተመለከተ መልስ ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

70. የቆዳ ፋብሪካን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ ላይ ትስስር የተፈጠረላቸው ፋብሪካዎች እንማን እንደሆኑ ያለመገለፁ የተጠየቀ ቢሆንም፤ ትስስሩ በደፈናው በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል ተፈፅሟል የሚል መልስ የተሰጠ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ይገልፃል፡፡

71. የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፈብሪካዎችን በተመለከተ በነበራዊ ሁኔታ የተሰጠ መልስ እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ጋር የግብዓት ትስስር ያላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት የገለፁ ሲሆን፤ እንደገና ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ከጂያንሲ ዛንግ ጋር ትስስር መፍጠራቸውን የገለፁ ቢሆንም ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበለውም፡፡

72. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት በሰጠው መልስ ትስስር መፍጠርን በተመለከተ በዋነኛነት የፋብሪካዎች ፍላጎት መሰረት በማድረግ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በየደረጃው የትስስር ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን፤እንዲሁም ድጋፍ አላገኘንም ካሉት 7 ጫማ ፋብሪካዎች 5ቱ( ጥቁር ዓባይ ፋብሪካ ከደብረብርሃን፣ፒኮክ ከድሬና ሞጆ፣ ካንጋሮ ከባቱ፣ፎንታኒና ከአዋሽና ከአቢሲኒያ እና ኒው ዊንግ ከኒው ዊንግ እህት ቆዳ ፋብሪካዎች) የሚያገኙ መሆኑን ገልፆ ሞደርን ዘጌ እና ኦኬ ጃማይካ ጥያቄ አቅርበው የማያውቁ መሆኑን ገልጿል፡፡

73. ይሁን እንጂ 7ቱ የጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩ የግብዓት(ቆዳ፣አክሰሰሪዎች፣ኬሚካሎች እና የመሳሰሉት)ን ከማግኘት አኳያ ድጋፍ በማድረግ በኩል የማመቻቸትና ትስስር ሥራ አልሰራም ባሉበት ሁኔታ የራሱን የሥራ ድርሻ ሳይወጣ በኦዲቱ ሂደት ወቅት ለኦዲቱ ቡድኑ ያልሰጠውን መልስ በረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት የኦዲት ቡድኑ በየፋብሪካው ተገኝቶ ለማጣራት ጊዜ ባለቀበት ወቅት ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ የቆዳ ግብዓትን ብቻ በተናጠል ትኩረት በመስጠት ከእህት ቆዳ ፋብሪካዎች ጋር ትስስር ያላቸው በመሆኑ ኢንስቲትዩቱን የሚጠይቁበት ሁኔታ አይኖርም ተብሎ የተሰጠውን መልስ የኦዲቱ ቡድኑ አግባብነት የሌለው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

74. በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመበት አላማ አንጻር እና ካዘጋጀው የደንበኞች ቻርተር አኳያ በአምራች ፋብሪካዎች መካከል የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት ትስስር መፍጠር ያለበት በመሆኑ ጥያቄ ሲያቀርቡ ብቻ ይስተናገዳሉ ተብሎ የተሰጠው መልስ በኦዲት ቡድኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ እንዲሁም እንጦጦ ቤተ- ዕደጥበብ ለቦርሳ ምርት የሚያስፈልገውን ያለቀለት ቆዳ ግብዓት ለማግኘት ከጂያንሲ ዛንግ ጋር ትስስር ስለማድረጉ ለኢንስቲትዩቱ በቀን 20/02/2010 ዓ.ም በቁጥር ወ.ደ/2010-02-20-2011 የተፃፈ ደብዳቤ በማስረጃነት ተያይዞ ቀርቧል የተባለውን የኦዲት ቡድኑ ያላገኘው መሆኑን ይገልፃል፡፡

75. በኢንስቲትዩቱ በጫማ ፣ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች እና በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬቶች በተሰጣቸው ተግባር ላይ በተመለከተው መሰረት በጥራት ላይ የተመሰረተ የግብዓትና ምርት ትስስር እንዲፈጠር በቆዳ ፋብሪካዎች፣ በጫማ ፋብሪካዎች እና በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች መካከል የምክክር ጊዜ እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑን፤ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው የተገልጋዮች ቻርተር የግብዓት አቅርቦትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና የግብዓት ትስስር መፍጠር የሚሉ በመሆናቸው ከዚህ አኳያ ኢንስቲትዩቱ የሚጠበቅበትን ሥራ ያልሰራ በመሆኑ ከፋብሪካዎቹ የሚጠበቅ ኢኮኖሚኖሚያዊ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የገበያ ጥናት፣ ማፈላለግና ትስስር መፍጠሩን በተመለከተ

76. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶች ሊያከናውን፤ እንዲሁም የገበያ ማፈላለግና ትስስር በመፍጠር የኤክስፖርት አፈፃፀሙን ሊያሳድግ ይገባል፡፡
77. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ምርት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቆይ እና ለማስተዋወቅ በተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች ለመግባት የሚያስችል የገበያ ልማት እስትራቴጂዎች ጥናት ከዚህ በታች የተመለከቱትን-
    1. በዩኒዶ የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ የአውሮፓ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ጥናት፣
    2. ወደ አሜሪካን ገበያ ለመግባት የተዘጋጀ የገበያ ፔኒትሬሽን(መግቢያ) ጥናት፣
    3. በታክት ሰርቪስ ፒ.ኤል.ሲ (TACT Service P.L.C) የተጠና በጫማና በቆዳ ውጤቶች ወደ ተወሰኑ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ገበያ ለመግባት የሚያስችል የገበያ እስትራቴጂ ጥናት፣
    4. በኮሜሳ (COMESA) ትብብር አማካኝነት የተካሄደ የቆዳ ንዑስ ዘርፍ የገበያ ጥናት እና የእሴት ሰንሰለት እስትራቴጂ ጥናቶች ያዘጋጀ መሆኑ ከማስረጃዎች መረዳት ተችሏል::
78. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ በተጠናው የገበያ እስትራቴጂ ጥናት መሰረት የገበያ ማፈላለግና ትስስር የፈጠረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ጫማ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡- 4ቱ የጫማ ፋብሪካዎች ( ካንጋሮ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) ድጋፍ ያላገኙ መሆናቸውን ሲገልፁ፤ ለ4ቱ (አንበሳ፣ ጥቁር አባይ፣ ፒኮክ እና ኦኬ ጀማይካ) ጫማ ፋብሪካዎች ድጋፍ የተደረገላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡
79. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት በሰጠው መልስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወንድና የሴት ቦርሳ ማስራት በመፈለጉ ከገበያ ትስስር አንፃር በደብዳቤ ቁጥር 02.1.3.9/22-

23 በቀን 17/04/2009 ዓ.ም ለሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካ የተላከ መሆኑን( ይህም ጫማን የማይገልፅ) እና በእ.ኤ.አ ሚያዚያ 19-30/2016 ጃፓን ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን ኤጀንሲ( JICA) ባዘጋጀው የንግድ ግንኙነት እንዲፈጠር ምርቶችን ማስተዋወቅ ትርዒት ላይ ሞደርን ዘጌና ፎንታኒና እንዲሳተፉ የተደረገ መሆኑ ቢገለፅም ሁለቱም ደብዳቤዎች በማስረጃነት ያልቀረቡ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ይገልፃል፡፡

80. እንዲሁም የኤክስፖርት አቅም ከፍ በማድረግ አገራችን በጫማ ረገድ ያላትን አቅም ከማስተዋወቅ አንፃር በተለይ የታወቁ ገዢዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት እና ምርቶችን በአሜሪካ ገበያ በማስታዋወቅ ለመሥራት በፕሮጀክት ደረጃ በፕሪሜትር ኮንሰልቲንግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኩል በሜድባይ ኢትዮጵያ እና በኢንስቲትዩቱ መካከል የኮንትራት ስምምነት በአራት የክፍያ ወቅት በሚፈፀም ክፍያ በጠቅላላው 500,000 የአሜሪካን ዶላር እ.ኤ.አ መጋቢት/2016 የኮንትራት ውል የተገባ ሲሆን በፕሮጀክቱ የተያዘው የኤክስፖርት ገቢ በውሉ መሰረት( በመጀመሪያ ዓመት 4.75 ሚሊዮን ዩኤስዲ፣ በሁለተኛው ዓመት 45 ሚሊዮን ዩኤስዲ፣ ሶስተኛ ዓመት 127.5 ሚሊዮን ዩኤስዲ፣ በአራተኛ ዓመት 229.5 ሚሊዮን ዩኤስዲ እና በአምስተኛው ዓመት 382.25 ሚሊዮን ዩኤስዲ ቢሆንም ከ 2009 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በፕሮጀክቱ የተያዘው የኤክስፖርት ገቢ ግብ በእቅድ በተቀመጠው መሰረት ሊከናወን አለመቻሉ የተመለከተ በመሆኑ፤ የኦዲት ቡድኑ ፕሮጀክቱ ችግር በገጠመው ወቅት ከተመደበለት በጀት ምንያህል ክፍያ ተከፍሎ እንደተቋረጠ እና በውሉ ላይ በተገለፀው መሰረት ምን ያህል ገቢ በአሜሪካን ዶላር እንደተገኘ እና በምን ሁኔታ እንደሚገኝ ለኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ መልስ አልተሰጠውም፡፡

81. ሆኖም የነበራዊ ሁኔታ መግለጫ በኦዲት ቡድኑ በቀረበበት ወቅት ኢንስቲትቱ በሰጠው መልስ ሜድ ባይ ኢትዮጵያ ያለበት ደረጃና የእቅድ አፈፃፀም በአሁኑ ወቅት ሪፖርት ተሰርቶ በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና የበላይ አመራሮች ከተገመገመ በኋላ የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ስለ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ አፈፃፀም ሪፖርት እንዲያቀርብ ታህሳስ 16/--- በደብዳቤ ቁጥር 03.2/1-4 (አመተ ምህረቱ ያልተጠቀሰ) ጥያቄ በኢንስቲትዩቱ የቀረበ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

82. በተጨማሪም የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካዎችን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 5 ፋብሪካዎች በኦዲት ወቅት የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ ኢንስቲትዩቱ የገበያ ማፈላለግና ትስስር የፈጠረላቸው ስለመሆኑ ባቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

- ለእንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ የገበያ ማፈላለግና ማስተሳሰርን በተመለከተ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ (ሰኔ 27/2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 01-11-619-38

በደረሰ ደብዳቤ በቻይና የንግድ ትርዒት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚል ደብዳቤ በነባራዊ ሁኔታ ወቅት ቀርቦ ታይቷል)

- ችባን ትሬዲንግ፣ ያምሮት ገ/መስቀል እና የዚችዓለም መዓዛ ኢንስቲትዩቱ የገበያ ማፈላለግና ትስስር ድጋፍ ያልሰጣቸው መሆኑን ሲገልፁ፤ የዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ኢንስቲትዩቱ የውጭ ባለሀብት መጥቶ እንዲጎበኝ ቢያደርግም ወደ ግዥ ሁኔታ እንዲለወጥ ያላደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት የዚች አለም መዓዛ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች አምራች ፋብሪካን በተመለከተ ነሃሴ 25/2010 ዓ.ም ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ጽ/ቤት በተፃፈ ደብዳቤ በጃፓን ኢንተርናሽናል ኮኦፐሬሽን ኤጀንሲ አማካኝነት በዓለም ገበያ ከማስተዋወቅ አንፃር በፈረንሳይ ፓሪስ በእ.ኤ.አ 4/09/2018 በሚካሄደው አለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ተሳትፎ እንዲያደርጉ የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍ አምራች ፋብሪካው በጠየቀው መሰረት ትብብር እንዲፃፍላቸው የሚል  ማስረጃ ቀርቦ የታየ ቢሆንም ይህ ማስረጃ ኢንስቲትዩቱ የገበያ ማፈላለግና ትስስር መፍጠሩን የማያመለክት በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የቀረበውን ማስረጃ አልተቀበለውም፡፡ እንዲሁም ሜድ ባይ ኢትዮጵያ ፕሮጀክትን በተመለከተ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በፕሮጀክቱ አማካኝነት ኤክስፖርት የተደረገው የምርት መጠን 8,928 ጥንድ ጫማ መሆኑ ተገልፆ ከዚህም የተገኘው ገቢ 166,805 የአሜሪካን ዶላር ነው ተብሎ ለተሰጠው መልስ ከመቼ ጀምሮ  እስከ መቼ እንደሆነ ጊዜውን የማያመለክ በመሆኑ  በኦዲቱ በተጠየቀው መሰረት መልስ ያልተሰጠበት በመሆኑ የተሰጠውን መልስ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

83. ስለሁኔታው ለኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች/ማኔጅመንት/  በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በጋራ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በአሁኑ ወቅት በቆዳ ምርቶች ገበያ ጠንካራ ውድድር መኖሩ፣ የገዢዎች ፍላጎት በፍጥነት የሚለዋወጥና ገበያውም ያልተረጋጋ በመሆኑ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት ከፍተኛ ጥረት እንደሚያስፈልግ በመለየቱ የኢንዱስትሪውን ምርቶች ለማስተዋወቅና በተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች ለመግባት ጥናቶቹ ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
84. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ከ2008- 2010 በጀት ዓመታት ከተዘጋጁት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ባገኘው መረጃ መሰረት የኢክስፖርት አፈጻጸሙ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
    - በ2008 በጀት ዓመት ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ ኢንዱስትሪ ዘርፍ 185 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 116.35 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን፤ይህም የእቅዱን 62.89% ሆኖ በ 2007 በጀት ዓመት አፈፃፀም ተገኝቶ ከነበረው 132.86 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጋር ሲነፃፀር የ 16.51 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (12.43%) ቅናሽ ያሳየ መሆኑ፣

- በ2009 በጀት ዓመት 272.70 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 115.46 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን፤ ይህም አፈፃፀሙ 42.34% ሆኖ ከ 2008 በጀት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር 0.89 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር(0.76%) ቅናሽ የታየ ሲሆን፣
- በ2010 በጀት ዓመት 280.53 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 133.77 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙ 47.69% በመሆኑ የኤክስፖርት ገቢው በሶስቱም ተከታታይ በጀት ዓመታት እየቀነሰ መሄዱ ኢንስቲትዩቱ የተጠኑትን ጥናቶች ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ክፍተት የሚታይበት መሆኑ ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶቹ በኦዲቱ ወቅት መረዳት ተችሏል፡፡

85. ኃላፊዎቹ በሰጡት መልስ የገበያ ስትራቴጂ ጥናቶቹ ተግባራዊ እየተደረጉ ነው ቢሉም፤ የኦዲት ቡድኑ ከ 2008- 2010 በጀት ዓመታት የተገኙትን የኤክስፖርት ገቢ መሰረት በማድረግ ውጤታማ ተግባር አለመከናወኑን ተገንዝቧል፡፡

86. በኢንስቲትቱ ገበያ ጥናት ዳይሬክቶሬት ተግባር ላይ በተቀመጠው መሰረት፡-

    1. ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶች ማከናወን፣
    2. የኢትዮጵያ ቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ያላቸውን ገበያ ጠብቀው እንዲቆዩ፣ አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለይተው በመግባት የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሰፉ፣ የምርት ስብጥራቸውን እንዲጨምሩ እና ለምርቶቻቸው ተገቢውን እና ከፍተኛውን ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ ቀጣይነት ያለው የገበያ ጥናት በማጥናት ተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
    3. በኢንስቲትዩቱ ተገልጋዮች ቻርተር ላይ የገበያ ጥናት አገልግሎት መስጠት እና የገበያ ማስተዋወቅና የማስተሳሰር ድጋፍ መስጠት ከሚሉት አንፃር ኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ ባለማድረጉ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የተጠኑት ወደ ተለያዩ ሀገራት የሚያስገቡ የገበያ ጥናት ስትራቴጂዎች ለፋብሪካዎች ያላደረሰ በመሆኑ እና በሚፈለገው ልክ የገበያ ማፈላለግና ትስስር ያልፈጠረ በመሆኑ ከ 2008- 2010 በጀት ዓመታት የተገኙ የውጭ ኤክስፖርት ገቢዎች ሊቀንሱ የቻሉ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ መረዳቱን ይገልፃል፡፡

87. ኢንስቲትዩቱ ከላይ የተገለፁትን ተግባራት በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ጥናት፣ የገበያ ማፈላለግና ትስስር በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኙ አለማድረጉ የውጭ ኤክስፖርት ገቢ መቀነስ ላይ የራሱን አሰተዋፆ እንዲኖር አድርጓል፡፡

## የማማከር አገልግሎትን በተመለከተ

88. ኢንስቲትዩቱ በምርት ናሙና፣ በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የማማከር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

89. ኢንስቲትዩቱ ከጥሬ ቆዳ እስከ ተለያየ የገበያ ፍላጎት ደረጃ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ምርት ባሉት የማምረት ሂደቶች ያሉትን የግብዓት፣ የምርት፣ የፍሳሽ ደረጃዎችን ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም የማዘጋጀት እንደአስፈላጊነቱም የመከለስ እና በቆዳ ፋብሪካዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች(አዋሽ፣ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ሲሆኑ፡- የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ቆዳ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡-

1. አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ የፍሳሽ ማጣሪያን በተመለከተ የተለያዩ የላቦራቶሪ የፍተሻ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን እና የተለያዩ የምርት ናሙናዎች በሚላክበት ወቅት ምርቱ ደረጃውን የጠበቀና ለኤክስፖርት ምርት የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላቱን የማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን፣
2. ባቱ ቆዳ ፋብሪካ፡- የተገለፁትን የምክር አገልግሎት ማግኘቱን፣
3. ብሉናይል ቆዳ ፋብሪካ፡- የምክር አገልግሎቱን አለማግኘቱን፣
4. ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፡- የምርትና የግብዓት ደረጃዎችን በተመለከተ የተወሰነ/በቂ የማይባል/ አገልግሎት መኖሩን ገልፀው፤ የፍሳሽ ደረጃዎችን በተመለከተ ጥሩ የምክር አገልግሎት መኖሩን፣
5. ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ አቅም ከመገንባት አኳያ አዲስ ቴክኖሎጂ በማምጣት በኩል ያደረገው የምክር እገዛ አለመኖሩ፣
6. ሞጆ ቆዳ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የማማከር ሥራ ያልሰራ መሆኑን፣
7. ገላን ቆዳ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ ተግባር ተኮር ስልጠና ያለመስጠቱን፣
8. ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትቱ የሰጠው የምክር አገልግሎት የሌለ መሆኑን፣
9. ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ፡- የግብዓትና የምርት አመራረት ደረጃዎች ክለሳ በተደረገበት ወቅት በኢንስቲትዩቱ እና በኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ በተደረገው ስልጠና የተሳተፉ መሆናቸውን ገልፀው የፍሳሽ ደረጃዎችን በተመለከተ የማማከር አገልግሎት ድጋፍ ያልተሰጠ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ በዚህ መሰረት አምስት ፋብሪካዎች(ብሉናይል ፣ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን እና ባህርዳር) ቆዳ ፋብሪካዎች የምክር አገልግሎቱን ያላገኙ ሲሆን፤ አዋሽ እና ባቱ ቆዳ ፋብሪካዎች የምክር አገልግሎት ማግኘታቸውን ሲገልፁ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካዎች በከፊል የማማከር አገልግሎት ያገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

90. የማማከር አገልግሎት ድጋፍ ያላገኙ ፋብሪካዎችን በተመለከተ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የሰጡት መልስ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

91. የነባራዊ ሁኔታ ለኢንስቲትዩቱ በቀረበበት ወቅት ውሃ አልባ በክሮም የማልፋት ቴክኖሎጂ፣ ለኮልባ በኤሌክትሮ ኦክስዴሽን የማጣራት ዘዴ እና በሞጆ፣ኮልባ እና በኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር የካይዘን ፍልስፍና ለመሞከር ታቅዶ በፋብሪካዎቹ ችግር ምክንያት አለመተግበሩን የማብራሪያ መልስ የሰጡ ቢሆንም በማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

92. እንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት የማማከር አገልግሎትን በተመለከተ ከቆዳ ግብዓት ጋር በተያያዘ የውሀ አልባ ማልፋት ቴክኖሎጂን ወደ ቆዳ ፋብሪካዎች ለማሸጋገር ከእ.ኤ.አ 2016 ጀምሮ በተለያዩ ቆዳ ፋብሪካዎች እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ የቆየ ስለመሆኑ ለአብነት በአዋሽ፣ በሞጆ፣ በኮልባ፣ በባቱ እና በባህር ዳር ቆዳ ፋብሪካዎች የገለፀ ሆኖ በማስረጃነት ውሃ አልባ ክሮም ማለስለሻ ቴክኖሎጂ ለኢትዮጵያ ቆዳ ፋብሪካዎች ከእ.ኤ.አ ታህሳስ 2016 ጀምሮ ለሁለት ዓመት የሚቆይ ሰነድ ያቀረበውን የኦዲት ቡድኑ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የውሃ አልባ ቆዳ ማልፋት ቴክኖሎጂ ከሙከራ ባሻገር በፋብሪካዎቹ ችግር ምክንያት ያልተተገበረ ስለመሆኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ኢንስቲትዩቱ ከሰጠው መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

93. ሆኖም ኢንስቲትዩቱ የማማከር አገልግሎትን መስጠት የሚገባው በአንድ ተግባር ላይ ባልዋለ ውሃ አልባ ማለስለሻ(ቴክኖሎጂ) ብቻ ሳይሆን፤ በግብዓት፣ በምርት እና የፍሳሽ ደረጃዎችን ከአለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም በማዘጋጀትና እንደአስፈላጊነቱም በመከለስ በቆዳ ፋብሪካዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በአንድ የቆዳ ግብዓት ላይ የተሰጠውን የውሃ አልባ ቴክኖሎጂን ብቻ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ሌሎችንም ከላይ የተጠቀሱትን(የምርት ናሙና፣ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቀ ምርት ባሉት ሂደቶች ያሉትን የግብዓት፣ የምርትና የፍሳሽ ደረጃዎችን ስልጠና) በማካተት የማማከር አገልግሎት መስጠት እንዳለበት የኦዲት ቡድኑ ያምናል፡፡

94. በኢንስቲትዩቱ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ተግባር ላይ በተመለከተው መሰረት ከጥሬ ቆዳ እስከ ተለያየ የገበያ ፍላጎት ደረጃ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ምርት ድረስ ባሉት ሂደቶች ያሉትን የግብዓት፣ የምርት፣ የፍሳሽ ደረጃዎችን ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም የማዘጋጀት፣ እንዳስፈላጊነቱም በመከለስ በቆዳ ፋብሪካዎች ሰርፀው እንዲገቡ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በተገልጋዮች ቻርተር ላይ የኢንዱስትሪ ማማከር አገልግሎት ይሰጣል ከሚሉት አንፃር ኢንስቲትዩቱ ለቆዳ ፋብሪካዎች የሚጠበቅበትን ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት መረዳት ችሏል፡፡

95. ኢንስቲትዩቱ በሥራ ተግባሩ እና በደንበኞች ቻርተር ላይ ያስቀመጣቸውን በምርት ናሙና፣ በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የማማከር አገልግሎት ተግባራትና ድጋፍ ለሁሉም ድጋፍ ለሚፈልጉ ፋብሪካዎች ካልሰጠ የሥራ ግዴታዎቹን በተሟላ ሁኔታ አለመወጣቱን ከማመልከቱም በላይ ፋብሪካዎች የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ምርት እንዳያመርቱ እና በፍሳሽ ልቀትም በኩል አካባቢ ላይ ብክለት እንዲያደርሱ ያደርጋል፡፡

## የምርትና የሰው ኃይል ልማት እና ምርምርን በተመለከተ

96. ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ሊሰራ፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ሊያከናውን፤ እንዲሁም በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ሊያግዝ ይገባል፡፡

97. ኢንስቲትዩቱ በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች

    1. አንበሳ ጫማ ፋብሪካ፡- የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ ከተለያየ ዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው በፋብሪካው ለተቀጠሩ 27 ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሮች ስልጠና በኢንስቲትዩቱ የተሰጠ ቢሆንም፤ የኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤት መተግበርን በተመለከተ መልስ ያልሰጡ መሆኑ፣
    2. ጥቁር ዓባይ ጫማ ፋብሪካ፡- የምርምር ውጤቶችን ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው ወርክ ሾፕ ያገኘ መሆኑን ቢገልፁም(በወርክ ሾፕ የተሳተፉበት ርዕስ) ያልተገለፀ መሆኑ፣
    3. ፒኮክ ጫማ ፋብሪካ፡- ምርምርን በሚመለከት አልፎ አልፎ የውጭ ኤክስፐርቶችን ከውጭ በማምጣት ኢንስቲትዩቱ የሚደግፍ መሆኑን፣
    4. ካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ፡- ከኢንስቲትዩቱ የደረሰው የምርምር ድጋፍ የሌለ መሆኑን፣
    5. ኦኬ ጃማይካ ጫማ ፋብሪካ፡- ከኢንስቲትዩቱ የደረሰው የምርምር ድጋፍ አለመኖሩን፣
    6. ኒው ዊንግ አዲስ ጫማ ፋብሪካ፡- ከኢንስቲትዩቱ የደረሰው የምርምር ድጋፍ አለመኖሩን፣
    7. ፎንታኒና ጫማ ፋብሪካ፡- በኢንስቲትዩቱ ጫማዎቻቸውን የሚያስፈትሹ መሆኑን እና ሥራቸውን የሚሰሩ መሆኑን፣
    8. ሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካ፡- ከኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤት ድጋፍ ያልደረሳቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ በዚህ መሰረት 5 ጫማ ፋብሪካዎች( አንበሳ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ እና ሞደርን ዘጌ) የምርምር ውጤት ድጋፍ ያልደረሳቸው

ሲሆን፤ 3ት ጫማ ፋብሪካዎች (ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ እና ፎንታኒና) ድጋፉን ያገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትብብር በመፍጠር የምርምር ሥራዎችን በማከናወን የምርምር ውጤቶችን በጫማ አመራረት ዘርፍ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች ለማስተላለፍ በባህርዳር እና በወሎ ዩኒቨርሲቲዎች በማከናወን ላይ የሚገኝ መሆኑን በመግለፅ በማስረጃነት የምርምር ርዕስ ቅፅ( የምርምር በጀት ምንጭ፣ የተማሪዎች ብዛት እና የምርምሩ ርዕስ) የሚያመለክት በማቅረብ ገልፀዋል፡፡

99. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተሰጠ መልስ የምርምር ውጤቶችን በጫማ አመራረት ዘርፍ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች ለማስተላለፍ ከባህርዳር እና ከወሎ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በቅንጅት በቀጣይነት እየተሰራ መሆኑን ገልፀው የምርምሮቹ ዝርዝር ከዚህ በፊት በቀረበው ቅፅ ላይ የተመለከተ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

100. ይሁን እንጂ የተሰጠው መልስ የምርምር ውጤቶቹ ወደፊት የሚተላለፉ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑን ከተሰጠው መልስ የኦዲት ቡድኑ መረዳት የቻለ መሆኑን ይገልፃል፡፡

101. በኢንስቲትዩቱ በ2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በተገለፀው መሰረት ሁለት የምርምር ሥራዎች 1ኛው Solar Mobile Leather Case for Cell-Phone charging 50%,and Production of dummy from chrome Shavings 75% የምርምር ሥራዎች ጅምር ክንውኖች የነበሩ መሆናቸው የተመለከተ ቢሆንም፤በ 2009 በጀት ዓመት  በመቋረጣቸው ለቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካዎች ውጤታቸው ያልተላለፈ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

102. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ተጀምረው የነበሩ 2/ሁለት/ የምርምር ሥራዎች ምርምሩን ሲያከናውኑ የነበሩ ባለሙያዎች በ 2009 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ማለትም ከነሀሴ ጀምሮ ለሁለት ዓመት (ከ 2009- 2010 ዓ.ም) ለትምህርት ወደ ህንድ ሀገር በመሄዳቸው ምክንያት ምርምሩ ሳይጠናቀቅ በነበረበት አፈፃፀም ላይ የሚገኝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

103. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ዳግመኛ ባቀረበው ቃለ-መጠይቅ በመነሻ ወቅት ለምርምር ሥራው ምን ያህል ብር በጀት እንደተያዘ፤እንዲሁም እስከተቋረጠበት ጊዜስ ምንያህል ብር ወጪ ተደረገ የሚል ቀርቦላቸው በሰጡት መልስ ከሀምሌ1/2007 እስከ ሰኔ 30/2008 የፕሮግራም በጀት አጠቃቀም በሚል ሰነድ በሂሳብ ኮድ 6223 የምርምርና ልማት አላቂ እቃዎች የሚል ሰነድ አቅርበው ሥራው በተቋረጠበት ሁኔታ ብር 150,000 (100%) ወጪ መደረጉን የሚያመለክት ማስረጃ ማቅረባቸው በኦዲቱ ማወቅ ተችሏል፡፡

104. በኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ተግባር ላይ በተመለከተው መሰረት በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ቴክኖሎጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ማድረግ የሚያስችል የምርምርና ስርፀት እንዲሁም የምርት ማልማት ሥራዎችን በፋሽን ዲዛይን፣ በቆረጣና ስፌት በየጊዜው በማካሄድ በተገኘው ውጤት መሰረት ዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚከታተል መሆኑን ከሚገልፀው አኳያ የምርምሩ መጀመር ጥሩ ሆኖ ሳለ ሳይጠናቀቅ የመቋረጡ መንስኤ ሌሎች የሚመለከታቸውን ሰራተኞች የማሳተፍ ችግር የነበረበትና በሁለት ሰራተኞች ላይ ብቻ ተወስኖ የተሰራ መሆኑን ኢንስቲትዩቱ በመገንዘብ የተሳትፎ አሰራር ስርዓት እንዲበረታታ ማድረግ ያለበት መ፤ሆኑን የኦዲት ቡድኑ ያምናል፡፡

105. ኢንስቲትዩቱ ባለው የምርምር የሰው ኃይል በተሳትፎ አሰራር ዘዴ ምርምሮችን እንዲሰሩ ካላደረገ ለኢኮኖሚ አስተዋፆ ሊያደርጉ የሚችሉ ምርምሮች ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡

106. በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ ኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤት ድጋፍ የሰጠ ስለመሆኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡-

- አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ፡- የኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤት ያልደረሰው መሆኑ፣
- ባቱ ቆዳ ፋብሪካ፡- ምርምር በሙከራ ደረጃ የተሰጠው መሆኑ ሲገለፅ (የምርምሩ ዓይነት ያልተገለፀ መሆኑ)
- ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን እና ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ ያደረጋቸው የምርምር ውጤቶች ድጋፎች ያልደረሳቸው መሆኑን ሲገልፁ፤ ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ በምርት ልማት እና በጥራት አመራር ድጋፍ ማግኘቱን ገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት 7ቆዳ ፋብሪካዎች የምርምር ውጤት ያልደረሳቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት አሳውቀዋል፡፡

107. እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የዋንኬ እና የአዳል በግ ቆዳዎችን የቆዳ ፋብሪካዎች ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ምርምር በማድረግ በሥራው ለተሰማሩ ወርክሾፕ በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ያደረገ መሆኑን የገለፀ ሲሆን፤ ምርምሩ በናሙና በተመረጡት ቆዳ ፋብሪካዎች ሥራ ላይ ስለመዋሉ የኦዲት ቡድኑ ለማረጋገጥ ለእያንዳንዱ የቆዳ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡-

1. አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ ወርክሾፕ ማዘጋጀቱን ገልፀው፤ ፋብሪካው ቀደም ብሎም ለጎልፍ መጫወቻ ምርት እያመረተበት የሚገኝ መሆኑ፣
2. ባቱ ቆዳ ፋብሪካ፡- ፋብሪካው የበሬ ቆዳ ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ መሆኑ፣
3. ብሉናይል ፋብሪካ፡- የፋብሪካው ሰራተኞች ወርክሾፕ ያልተሳተፉ መሆኑ፣
4. ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፡- ኢንስቲትዩቱ በወርክ ሾፕ ያላሳተፈ መሆኑን፣

5. ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ፡- የተጠቀሰው ወርክ ሾፕ የምርምር ውጤት ለፋብሪካው ያልደረሰው ሲሆን፣ የዋንኬ እና አዳል በግ በአጠቃላይ መጠኑ ሲታይ ከ 10% የማይበልጥ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ ቅድሚያ መስጠት የነበረበት 90% የሃይላንድ ሌጦ ችግር ላይ መሆን ሲገባው ለዋንኬ ትኩረት መስጠቱ ተገቢ አለመሆኑን የገለፁ መሆኑ፣
6. ሞጆ ቆዳ ፋብሪካ፡- ድርጅቱ ሥራ ላይ ያዋለው የዋንኬ እና የአዳል በግ ሌጦ አለመኖሩ፣
7. ገላን ቆዳ ፋብሪካ፡- ፋብሪካው ወርክሾፕ ላይ ያልተሳተፈ ቢሆንም፣ቀደም ሲል ለሀገር ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ምርቶች ሲያውል የቆየ መሆኑን ገልፀው ለውጭ ኤክስፖርት የማይሆን ሲሆን፣ምክንያቱም የጥራት ደረጃው ከደጋው እና ከወይና ደጋው ጋር ሲወዳደር ደረጃው ዝቅተኛ በመሆኑ፣
8. ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ፡- ዋናው ጥሬ ቆዳ እጅግ በከፋ ሁኔታ ደረጃ ላይ እያለ በዋንኬ እና በአዳል በግ በምን መልኩ ወርክሾፕ እንደተዘጋጀ የማያውቁ መሆኑን፣
9. ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ፡- በወርክሾፑ ላይ የተሳተፉ መሆናቸውን ገልፀው ሌጦዎቹንም ሥራ ላይ ያዋሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከ 9ኙ ቆዳ ፋብሪካዎች 6ቱ በወርክሾፑ ያልተሳተፉ ሲሆኑ፣ 2 ቱ በወርክ ሾፑ ላይ መሳተፋቸውን የገለፁ ሆኖ ቀሪው አንዱ በበሬ ቆዳ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በተሰጠው መልስ ታውቋል፡፡

108. ኢንስቲትቱ ምርምሩ ተቀባይነት እንዲያገኝ በቆዳው ዘርፍ ቴክኖሎጂ ተሰማርተው ለረጅም ዓመታት የሰሩ እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በምርምር ሂደቱ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሊያደርግ የሚገባ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ካደረገው የመስክ ቃለ-መጠይቅ ተገንዝቧል፡፡

109. ኢንስቲትቱ ለሚያደርጋቸው የቆዳው ዘርፍ ምርምሮች በሙያው ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎችን በተሳትፎ እንዲካተቱ የማያደርግ ከሆነ የምርምር ውጤቱ የመቃኘት እድሉ አናሳ በመሆኑ አተገባበሩ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

110. ስለሁኔታው የኢንስቲትቱ የሥራ ኃላፊዎች/ማኔጅመንት/ የኦዲት ቡድኑ በጋራ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በ 2008 በጀት ዓመት ከከፍተኛ ተቋማት ጋር ባለው ቁርኝት መርሃ-ግብር መሰረት ለንዑስ ዘርፉ አመራሮች እና ባለሙያዎች በሶፍት ስኪል እና ዓይነት ስልጠና በመሰጠቱ ምክንያት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተመረቁ ባለሙያዎች ወደ ፋብሪካዎች እንዲቀላቀሉ ድጋፍ የተደረገ መሆኑን ሲገልፁ፣ በ 2009 በጀት ዓመት የቴክኖሎጂ እና የአቅም ውስንነትን ለመፍታት ተከታታይ ሥራ እና ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ከዚህ አንፃር የአሰራር ዘዴን ለመሻሻል በቤንች ማርኪንግ እና በካይዘን የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ወደ ዘርፉ ተሰማርተው የስልጠና ድጋፍ እየሰጡ መሆኑን ገልፀው ከሰው ኃይል አቅም ጋር በተያያዘ የአጫጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች በኢንስቲትዩቱ እና በከፍተኛ ትምህርት

ተቋማት እየተሰጡ መሆኑን፤ እንዲሁም ፋብሪካዎች የማምረት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ መሳሪያዎችን እንዲገዙ ከኢሲኤፍ ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር የመሳሪያ ግዥ እንዲፈፅሙ ድጋፍ የተደረገ መሆኑን አሳውቀው በ 2010 በጀት ዓመት ለማሳያ በአዲስ አበባ ቆዳ ፋብሪካ የካይዘን ፍልስፍና በመተግበር የአሰራር ለውጥ እንዲኖር የተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

111. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ከሶስቱ ተከታታይ ዓመታት የኤክስፖርት ገቢ አንፃር ሲታይ ተሰራ የተባለው የማኔጅመንት እና ቴክኖሎጂ አቅምን የመገንባትና የማጠናከር ሥራ ተጨባጭ ውጤት እንዳላመጣ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

112. ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው ዓመታዊ እቅድ መሰረት ከደንበኞቹ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ኃላፊነትን ያስገነዘበ ቁርኝት ፈጥሮ የቴክኖሎጂ እና የአቅም ውስንነት ችግሮችን ለመፍታት ካልሰራ ሀገሪቷ የምትጠብቀወን የውጭ ኤክስፖርት ገቢ ከፍ የማድረግ ድርሻ እንዳይወጣ ያደርገዋል፡፡

## ለጥሬ ቆዳ ግብዓት የሚደረግ ጥንቃቄን በተመለከተ

113. ኢንስቲትዩቱ በበዓላትና በአዘቦት ወቅት የእንስሳት እርድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች የጥሬ ቆዳ ግብዓት በእርድ ወቅት ጥንቃቄ እንዲደረግለት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማስተዋወቅ (ፕሮሞሽን) ሥራ ሊሰራ እና በቆዳ አሰባሰብ ሂደትም የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

114. ኢንስቲትቱ በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- ነሀሴ 19/2009 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በተላከ ደብዳቤ ቁጥር 02.1/4/912 መሰረት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንዑስ ዘርፍ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሄዎችን ስለማቅረብ በሚል ርዕስ የብሄራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ካውንስል የኤክስፖርት እቅድ እያሽቆለቆለ መምጣቱን ተከትሎ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት አዲስ የአሰራር አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን ተከትሎ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት አያያዝና ግብይት ዙሪያ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን ለመፍታት የተዘጋጀ የድርጊት መርሃ-ግብር በሚል ስር ኢንስቲትዩቱ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ጋር በፈፃሚ አካልነት ተመድቦ ስለሰራቸው ሥራዎች በኦዲቱ ቡድኑ

ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ በአጋርነት የሚሰራ መሆኑ ቢገለፅም፤ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

115. የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ለኢንስቲትዩቱ በቀረበበት ወቅት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማስተዋወቅ (ፕሮሞሽን) ሥራ ስለመሰራቱ ኢንስቲትዩቱ ለመገናኛ ብዙሃን ያቀረባቸውን ሁለት ደብዳቤዎች ቀርበው የኦዲት ቡድኑ መመልከት የቻለ ሲሆን በቆዳ አሰባሰብ ሂደት የተሰጠ የቴክኒክ ድጋፍን የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

116. ለኢንስቲትዩቱ ረቂቅ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት በጥሬ ቆዳና ሌጦ አሰባሰብ ላይ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ በተሰጠ መልስ ሥራው የሚከናወነው በግብርና ሚኒስቴርና በየክልል ባሉ እንስሳት ሀብት ልማት ቢሮዎች መሆኑ ተገልፆ ኢንስቲትዩቱ የግብርና ሚኒስቴር በሚያመቻቸው መድረኮች ላይ በመገኘት በጋራ በሚሰሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ በቅርበት በመገኘት የሚሰራ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለኢንስቲትዩቱ በተላከ ደብዳቤ ላይ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ጋር በፈጻሚ አካልነት በቆዳ አሰባሰብ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጥ የተሰጠውን ሥራ ስለመሥራቱ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

117. በተጨማሪም በእርድ ወቅት የቆዳ ጥራት ተጠብቆ ገፈፋ እንዲካሄድ የቆዳና ሌጦ መግፈፊያ ቴክኖሎጂ በቄራዎች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ቴክኖሎጂው ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ ኢንስቲትዩቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በፈፃሚ አካልነት የተመደበ ቢሆንም፤ በኦዲቱ በናሙና በተመረጠው የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት የኦዲት ቡድኑ ኢንስቲትዩቱ ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በድርጅቱ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር በተሰጠ መልስ በኢንስቲትዩቱ የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

118.ስለሁኔታው የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ጥሬ ቆዳ እና ሌጦ አቅርቦት፣ ጥራት እና ግብይት በተመለከተ በዋናነት ኃላፊነቱን የሚወስደው ግብርና ሚኒስቴር ወይም እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሲሆን፤ ከኢንዱስትሪው ፍላጎት በመነሳት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በቅርበት እየተሰራ በተለያዩ ወርክሾፖች እና ስልጠናዎች ላይ በመሳተፍ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ባለሙያ በመመደብ እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

119. ኃላፊው ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሰራን ነን ቢሉም፤ የተሰራውን ሥራ የሚያመለክት ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

120. ኢንስቲትዩቱ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠው ወቅት በበዓላት ለሚደረግ እርድ ለቆዳ ጥንቃቄ እንዲደረግ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ እና ለፋና ብሮድካስቲንግ በቁጥር 02-1-7-3/5-10 በቀን ታህሳስ 26/2011 ዓ.ም የተላከ የዜና መግለጫ አቅርቦ በኦዲት ቡድኑ የታየ

ሲሆን፤ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በተለያዩ ወርክ ሾፖች እና ስልጠናዎች የተደረገ ተሳትፎንና የባለሙያ ምደባን የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

121. የቆዳና ሌጦ መግፈፊያ ቴክኖሎጂ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በቄራዎች ውስጥ ጥቅም ላይ ማዋልን በተመለከተ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት መልስ የኢንስቲትዩቱ ተግባር ሳይሆን የግብርና ሚኒስቴር ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡





ጥራቱን ያልጠበቀ ቆዳ በሀበሻ እና በኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር ቆዳ ፋብሪካዎች

## በግብርና ሚኒስቴር የተሰራ የግንዛቤ ማስጨበጫ

122. በግብርና ሚኒስቴር የግብይት ዳይሬክቶሬት ከጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የህግ ማዕቀፍ አንፃር ለክልሎችና በየደረጃው ለሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት፣ ለግብዓት ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ ሲሆን፡-

- በ 2008 በጀት ዓመት የቀድሞው የእንስሳትና ዓሳሀብት ሚ/ር በአዲስ መልክ እየተደራጀ ስለነበር የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ያልሰራ መሆኑ፣
- በ 2009 በጀት ዓመት ለደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልል አርባ ምንጭ ከተማ ላይ 100፣ ለኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ ላይ 370፣ አማራ ክልል መተማና ወልዲያ ከተሞች ላይ 280፣ ትግራይ ክልል ሁመራ ከተማ ላይ 52 በድምሩ 802 ተሳታፊዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ደረጃ ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉ፣
- በ 2010 በጀት ዓመት ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ ለ 96 ተሳታፊዎች በሞጆ ከተማ ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፤በአጠቃላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱን የአሰልጣኞች ስልጠና በመውሰድ ክልሎችና ከተማ

መስተዳድሮች በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላትና የግብይት ተዋንያን ስልጠና እየሰጡ የሚገኙ ስለመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለግብርና ሚኒስቴር የግብይት ዳይሬክቶሬት ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

123. በኢንስቲትዩቱ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት የሥራ ተግባር ላይ በተመለከተው መሰረት በጥራት ላይ የተመሰረተ የግብዓትና ምርት ትስስር እንዲፈጠር በቁም፣ በእርድና ከእርድ በኋላ በቆዳ እንክብካቤ የስልጠና፣ የማማከር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት የማስተባበር ተግባር የማከናወን ሥራ እንደሚሰራ ከተገለፀው አንፃር የግብርና ሚኒስቴር ተግባራት ናቸው ተብለው በዳይሬክተሩ የተሰጡትን መልሶች ከሥራ ተግባራቸው ጋር እንዲያገናዝቡ የኦዲት ቡድኑ ያስገነዝባል፡፡

124. ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት የሚገባውን ሥራ ካልሰራ በሚያደርጋቸው ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## የምርት እቅድ፣ ምርት ማምረት ሂደትና ጥራት ቁጥጥርን የማማከር አገልግሎት በተመለከተ

125. ኢንስቲትዩቱ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ለተሰማሩ የኢንዱስትሪ ባለሀብቶች በምርት እቅድና በምርት ማምረት ሂደት እና ጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

126. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- ኢንስቲትዩቱ ለፋብሪካዎች በስትራቴጂክ እቅድ መሰረት የእቅድ ሥራዎች የሚሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከእቅድ አዘገጃጀትና እቅድ አፈፃፀም (2008- 2010) በጀት ዓመታት ሪፖርት መረዳት የተቻለ ቢሆንም፤ በኦዲቱ በናሙና ለተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች (አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘኔ)፣ እና 9 ቆዳ ፋብሪካዎች (አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) በምርት ማምረት ሂደት እና በጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት ሥራ ስለመሥራቱ በማስረጃ ያልተገለፀ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

127. ኢንስቲትዩቱ በእቀድ፣ በምርት ሂደትና በጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት የሰጠ ስለመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የጫማ ፋብሪካ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ የተሰጡ መልሶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. አንበሳ ጫማ ፋብሪካ፡- በ 2009 በጀት ዓመት በቆዳ ውጤቶች ዝግጅት ላይ የማደራጀት ጥናት እና ምርታማነት የማሳደግ አገልግሎት ድጋፍ ያገኙ መሆኑን ገልፀው በእቅድ አዘገጃጀት ላይ ድጋፍ ያላገኙ መሆኑ፣

2. ፒኮክ ጫማ ፋብሪካ፡- በምርት ጥራት ቁጥጥር የምክር አገልግሎት ማግኘታቸውን ገልፀው በእቅድ አዘገጃጀት ላይ ድጋፍ ያላገኙ መሆኑ፣
3. ካንጋሮ፣ 4. አኬ ጃማይካ፣ 5.ኒው ዊንግ አዲስ፣ 6. ፎንታኒና እና 7. ሞደርን ዘኔ ጫማ ፋብሪካዎች በምርት ጥራት ቁጥጥር እና በእቅድ አዘገጃጀት ላይ የምክር አገልግሎቱን ድጋፍ ያላገኙ መሆናቸውን ሲገልፁ፤ ጥቁር ዓባይ ጫማ ፋብሪካ የምርት ጥራት ቁጥጥር እና የእቅድ አዘገጃጀት የምክር ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፤ በዚህ መሰረት አንድ ጫማ ፋብሪካ ሁለት ድጋፎች ያገኘ ሆኖ ሁለት የጫማ ፋብሪካዎች እያንዳንዳቸው አንድ ድጋፍ ማግኘታቸውን ሲገልፁ 5 ጫማ ፋብሪካዎች ሶስቱንም የማማከር አገልግሎት ድጋፎች ያለገኙ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በተሰጡ መልሶች ታውቋል፡፡

128. ኢንስቲትዩቱ ለሁለት ቆዳ ፋብሪካዎች ለሞጆ እና ለሀበሻ ቆዳ ፋብሪካዎች የማማከር አገልግሎት ድጋፉን የሰጠ ሲሆን ለቀሩት 7 ፋብሪካዎች ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት የኦዲቱ ቡድኑ ለሥራ ኃላፊዎች ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ታውቋል፡

129. ስለሁኔታው ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች/ማኔጅመንት/ የኦዲት ቡድኑ በጋራ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የኢንስቱትዩቱ ዓላማ ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ተወዳዳሪና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት በመሆኑ በየ5 ዓመቱ እስትራቴጂክ እቅድ የሚያዘጋጅ ሲሆን፤ በሀገር ደረጃ ሲፀድቅም ወደ ሥራ የሚገባ መሆኑን በመግለፅ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ የተቀመጡት ኤክስፖርት ግቦችን ለማሳካት በየፋብሪካዎች ግብ በመጣል ከመንግስት በሚሰጠው ድጋፍ ተዘርዝሮ የሚታቀድ ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ የንዑስ ዘርፉን እንዲያዘጋጅ እና አፈፃፀሙን እንዲከታተል በብሄራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ አቅጣጫ የሚሰጠው በመሆኑ፤በዚህ መሰረት የሚያቅድ ሲሆን፤በእቅድና አፈፃፀሙ ላይ የፋብሪካ ኃላፊዎች እንዲሳተፉ የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

130. ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በእቅድ ላይ የሚሰሩ ሥራዎችን አብራርተው የገለፁ ሲሆን በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ ከላይ ለተዘረዘሩት ቆዳ ፋብሪካዎች በምርት ማምረት ሂደትና በጥራት ክትትል የተሰሩ የማማከር ሥራዎችን የሚያመለክቱ ማስረጃዎችን በማቅረብ መልስ አልሰጡም፡፡

131. ኢንስቲትዩቱ የነበራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው መልስ ከ 2008- 2010 በጀት ዓመታት በምርት እቅድና በጥራት ቁጥጥር ለአንበሳ፣ ለፒኮክ፣ ለጥቁር ዓባይ ጫማ ፋብሪካዎች የአቅም ግንባታ ድጋፍ መሰጠቱን፤ እንዲሁም በምርት ሂደትና ጥራት ቁጥጥር ከ ታህሳስ 15-26/2011 ዓ.ም ስልጠና አዘጋጅቶ ለ 11 ፋብሪካዎች ጥሪ ያቀረበ ሲሆን በስልጠናው 7 ቆዳ ፋብሪካዎች የተሳተፉ መሆኑ ቢገለፅም ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

132. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት ለኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር በምርት እቅድና ቁጥጥር እንዲሁም በቆዳ ክምችት ቁጥጥር ሶፍት ዌር/ታነሪ ኢንቬንተሪ ኮንትሮል/ እንዲሁም ለአዋሽ ፋብሪካ በማሽን ኦፕሬሽንና አያያዝ እና የበቆዳ ክምችት ቁጥጥር ሶፍት ዌር የማማከር አገልግሎት የሰጠ መሆኑን ቢገልፅም በማስረጃ ያልተደገፈ ሲሆን፤በምርት ሂደት ጥራት ቁጥጥር በኦዲቱ ማጠናቀቂያ ወቅት ከ 22/04/2011 እስከ 26/04/2011 ዓ.ም ከተለያዩ ቆዳ ፋብሪካዎች ለተውጣጡ (የፋብሪካዎቹ ስም ላልተገለፁ) ስልጠና መስጠቱን ከቀረበው ሰዓት መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ(15 ሰልጣኞች) የሰለጠኑ ስለመሆኑ መመልከት ተችሏል፡፡

133. በኢንስቲትዩቱ መጋቢት/2007 ዓ.ም በተዘጋጀው የደንበኞች ቻርተር ላይ በተመለከተው መሰረት ከሚሰጡ ድጋፎች አንዱ የኢንዱስትሪ ማማከር አገልግሎት በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ ፋብሪካዎች በምርት ሂደትና በጥራት ክትትል የማማከር አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡

134. ኢንስቲትዩቱ በምርት ማምረት ሂደትና በጥራት ክትትል የማማከር ድጋፍ ካልሰጠ አምራች ፋብሪካዎች ለኤክስፖርት የሚያቀርቧቸው ምርቶቻቸው ከጥራት አኳያ ተፈላጊ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ የኤክስፖርት ገቢ እንዲቀንስ አስተዋፆ ያደርጋል፡፡

## የላቦራቶሪ ፍተሻ ድጋፍን በተመለከተ

135. ኢንስቲትዩቱ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች እስታንዳርዳቸውን ጠብቀው በጥራት የተመረቱ ስለመሆናቸው የላቦራቶሪ ፍተሻ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

136. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ ለ3ቱ(ፒኮክ፣ ካንጋሮ እና ሞደርን ዘጌ) ጫማ ፋብሪካዎች የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት የሰጠ ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

137. እንዲሁም የድጋፍ አሰጣጡን በተመለከተ ፒኮክ፣ ኦኬ ጃማይካ እና ሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በክፍያ አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ድጋፍ ሰጥቷል ማለት የማያስችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

138. ድጋፍ ስላላገኙት 3ቱ ፋብሪካዎች የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ የጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ ከ (2008- 2010 በጀት ዓመታት) ድጋፍ ስለመሰጠቱ መልስ ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

139. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ ቁጥር 16 ላይ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደ አግባቡ ክፍያ መጠየቅ የሚችል መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም፣ ይህንን እንደ አግባቡ ክፍያ መጠየቅ የሚል ፅንሰ ሀሳብ ለድጋፍ ጠያቂ ደንበኞቹ በማስረዳት በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጠር ያደረገ ስለመሆኑ

ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ መልስ ያልተሰጠ መሆኑ የኦዲት ቡድኑ ያስገነዝባል፡፡

140. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች የሚሰጣቸው የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎቶች በመደበኛ ሥራነት የሚመደቡ በመሆኑ ለሁሉም ፋብሪካዎች መሰጠት ያለበት መሆኑን የኦዲት ቡድኑ የሚያምን ሲሆን ከአገልግሎት ክፍያ አንፃር ድጋፍ ፈላጊ ፋብሪካዎችን በማወያየት መተማመን ላይ የተደረሰበት ክፍያ ቢጠየቅ የሚያግባባ እንደሚሆን የኦዲት ቡድኑ ያምናል፡፡

141. የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸው ምርቶች በክፍያ ጫናም ሆነ በተነሳሽነት ችግር በኢንስቲትዩቱ የላቦራቶሪ ፍተሻ ሳያደርጉ ኤክስፖርት ካደረጉ በጥራት ጉድለት ምክንያት ተፈላጊነት በማጣት ገበያ የማያገኙ ይሆናል፡፡

## የማሽን እና የባለሙያ እገዛን በተመለከተ

142. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ እና ቆዳ አልባሳት ከዲዛይን እስከ ማጠናቀቅ የማሽን አገልግሎት እና የባለሙያ እገዛ ሊሰጥ ይገባል፡፡

143. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡- 4ቱ (ጥቁር አባይ፣ ፒኮክ፣ ኦኬ ጃማይካ እና ፎንታኒና) ጫማ ፋብሪካዎች የማሽን እና የባለሙያ እገዛ ያገኙ መሆናቸውን ሲገልፁ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ ማሽነሪን በሚመለከት ከኢንስቲትዩቱ የቀበቶ ቀለም መቀቢያ እገዛ ቢጠይቅም የማሽን እጥረት አለ በማለት ድጋፍ ያላገኘ መሆኑን ገልፆ ነገር ግን በባለሙያ ደረጃ በ2009 ዓ.ም በቦርሳ ሥራ ላይ እገዛ የተደረገላቸው መሆኑን ገልፀዋል፤ እንዲሁም ካንጋሮ እና ኒው ዊንግ አዲስ ጫማ ፋብሪካዎች የማሽንም ሆነ የባለሙያ እገዛ ያላገኙ መሆናቸውን ሲገልፁ ሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካ አገልግሎቶቹን በክፍያ ማግኘቱን ገልጿል፡፡

144. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በናሙና ከተመረጡት ጫማ ፋብሪካዎች ውስጥ ለጥቁር ዓባይ፣ ካንጋሮ፣ ፒኮክ፣ ለፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ በድምሩ ለአምስት ፋብሪካዎች ድጋፉን የሰጡ መሆኑን ሲገልፁ ለቀሩት ሶስት ፋብሪካዎች አንበሳ፣ ኦኬ ጃማይካ እና ኒው ዊንግ አዲስ መልስ አልተሰጠም፡፡

145. ኢንስቲትዩቱ ለኦኬ ጃማይካ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የፓተርን ግሬዲንግ ማሽን እና ባለሙያ እገዛ መስጠቱን የገለፀ ቢሆንም በማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

146. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት ለአብነትም ለኦኬ ጀማይካ ጫማ ፋብሪካ በ09/01/2010 ዓ.ም ሞዴል እንዲባዛ ድጋፍ የተጠየቀበት እና ለካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ በቀን ግንቦት2/2008 ዓ.ም የካድካም አገልግሎት ድጋፍ ስለመጠየቅ የሚል የቀረቡ ደብዳቤዎችን በማስረጃነት ያቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተመለከተ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ ድጋፎችን ስለመስጠቱ የሚያመለክት ማስረጃ አያይዞ ያላቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

147. ኢንስቲትዩቱ ድጋፍን በተመለከተ በየበጀት ዓመቱ የፍላጎት መጠየቂያ ሰነድ ለእያንዳንዱ ፋብሪካ በማሰራጨት እንዲሞሉ በማድረግና ስለሁኔታውም የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በመሥራት የማይሰራ ከሆነ ድጋፍ ፈላጊ ፋብሪካዎች ማግኘት የሚገባቸውን ድጋፍ የማያገኙ ይሆናል፡፡

## ኤክስፖርት እስታንዳርድ የሆኑ የለሙ ምርቶችን ድጋፍ የሰጠ መሆኑን በተመለከተ

148. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ፣ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች የምርት ማልማት/ኤክስፖርት እስታንዳርድ ዲዛይኖች/ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

149. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና የተመረጡት 8 ፋብሪካዎች( አንበሳ፣ ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) ሲሆኑ፡- የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡-

1. አንበሳ ጫማ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ ከስልጠና ጋር የተዛመደ የምርት ልማት ሥራ የሰራ መሆኑ፣
2. ጥቁር ዓባይ ጫማ ፋብሪካ፡-የምርት ማልማትም ሆነ የቤንች ማርክ ሥራ ስልጠና ያገኙ መሆኑ፣
3. ፒኮክ ጫማ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ የምርት ማልማት ሥራ የሰራ ቢሆንም፤የቤንች ማርክ ሥራ ያልሰራ መሆኑ፣
4. ካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ በተወሰነ መልኩ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን፤ ይህም ስልጠና ኤክስፖርት ተኮር ሳይሆን መደበኛ የሥራ ላይ ልምምድ (ቆረጣ እና ስፌት) ስልጠና ለሰራተኞች የሚሰጥ ቢሆንም፤ ሰርተፊኬት የማይሰጡ ሲሆን የሚጠይቁት

ክፍያዎች ተገቢ አለመሆናቸውን ገልፀው በተጨማሪም በ 2003 እና 2004 ዓ.ም የቤንች ማርኪንግ ሥራ ይሰሩ የነበረ ቢሆንም፤ ከ 2008 -2010 ዓ.ም ምንም ዓይነት የቤንች ማርኪንግ ሥራ ያልሰሩ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

5. ኦኬ ጃማይካ ጫማ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትዩቱ የምርት ማልማት ስልጠናም ሆነ የቤንች ማርክ አገልግሎት ያልሰጠ መሆኑ፣
6. ኒው ዊንግ አዲስ ጫማ ፋብሪካ፡-ኢንስቲትዩቱ የምርት ማልማት ስልጠናም ሆነ የቤንች ማርክ አገልግሎት ያልሰጠ መሆኑ፣
7. ፎንታኒና ጫማ ፋብሪካ፡- በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ መልስ ያልሰጠ መሆኑ፣
8. ሞደርን ዘጌ ጫማ ፋብሪካ፡- ኢንስቲትቱ በክፍያ የምርት ማልማት ፓተርኖችን የሚሰጥ በመሆኑ ድጋፍ ሊባል የማይገባ መሆኑን በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

በዚህ መሰረት ኢንስቲትዩቱ ለአራት ጫማ ፋብሪካዎች( ካንጋሮ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ እና ሞደርን ዘጌ) የምርት ማልማት ሥራ ድጋፍ ያልሰጠ ሲሆን፤ለአራት ፋብሪካዎች ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት የሥራ ኃላፊዎቹ በሰጡት መልስ ታውቋል፡፡

150. በነባራዊ ሁኔታ ወቅት በኢኒስቲትዩቱ በተሰጠ መልስ ለአንበሳ፣ ለፒኮክ፣ ለኦኬ ጃማይካ እና ለካንጋሮ የቤንች ማርኪንግ ድጋፍ የተሰጠ መሆኑን ታውቋል፡፡

151. ሆኖም የተሰጠው መልስ የለማ ምርት/ኤክስፖርት ስታንዳርድ/ ስለመሆኑ የማይገልፅ በመሆኑ በኦዲት ቡድኑ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

152. ኢንስቲትዩቱ ረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት በኤክስፖርት ረገድ የጫማ ኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የቤንች ማርኪንግ ትግበራ በተመረጡ ሰባት ጫማ ፋብሪካዎች (በራምሴ፣ በጥቁር ዓባይ፣ በአንበሳ፣ በካንጋሮ፣ በጃማይካና በራስ ዳሽን ፋብሪካዎች) ከ 2008 በጀት ዓመት በፊት ከህንድ ተዋቂ ተቋማት ከመጡ ባለሙያዎች እና በኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች በጋራ በአሰራር ስርዓት፣ በምርት ሂደት፣ በጥራት ቁጥጥር፣ በምርት ማልማት፣ በጥገናና እንዲሁም በማኑዋል ዝግጅት ዙሪያ ተግባራዊ መደረጉን የገለፁ ቢሆንም ዝግጅቱ በተግባር ውጤታማ ሆኖ ለጫማ ፋብሪካዎቹ እክስፖርት ስታንዳርድ የለሙ ምርቶችን እንዲያገኙ ስለመደረጉ ያልተገለፀ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተደረገውን ሙከራ በውጤት ያልተደገፈ መሆኑን ይገነዘባል፡፡

153. በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡት 5 የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካዎች 4ቱ (እንጦጦ ቤተ-ዕደጥበብ፣ ያምሮት ገ/መስቀል፣ የዚችዓለም መዓዛ እና ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች) የለማ ምርት/ኤክስፖርት እስታንዳርድ/ አገልግሎት ድጋፍ ያላገኙ ሲሆን ችባን ትሬዲንግ የለማ ምርት አገልግሎት ያገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

154. ለኢንስቲትዩቱ ረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት  የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎችን በተመለከተ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡት ውጪ( ሩት ግርማይ፣ የምስራች ሀይሉ፣ሀና ብርሃነ እየሱስ..፣) ለተባሉ ድርጅቶች የለማ ምርት የተሰጠ መሆኑን ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የገለፀ ቢሆንም በኦዲቱ በናሙናነት ያልተካተቱ በመሆናቸው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

155. በኢንስቲትዩቱ በጫማ/ቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች  ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬቶች ተግባር ላይ የጫማ/የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች  አመራረት ቴክኖሎጂን ዓለም በደረሰበት ደረጃ በዋጋ፣ በጥራትና ምርታማነት ተወዳዳሪ ሊያደርግ የሚችል በምርት ልማት፣ በቴክኖሎጂ ልማት፣በጥራት ሥራ አመራር እና በሌሎች ችግር ፈቺና ወደ ተግባር ሊለወጥ የሚችል ምርምርና ጥናት በማካሄድ በተገኘው ውጤት መሰረት ዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ በመጠንም ሆነ በጥራት የቤንች ማርኪንግ ሥራዎችን ያከናውናል ከሚለው አኳያ ኢንስቲትዩቱ በተወሰኑ ፋብሪካዎች ብቻ እንዲተገበር ከማድረግ ውጪ ሁሉም ፋብሪካዎች ከኤክስፖርት አይታ አንፃር የለማ ምርት የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ድጋፍ በማድረግ ሊያበረታታ የሚገባ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ያስገነዝባል፡፡

156. ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ምርታቸው ከኤክስፖርት አንፃር ተወዳዳሪ ሆኖ ገበያ በማግኘት ለሀገሪቱ ገቢ እንድታገኝ ማድረግ በመሆኑ የለሙ ምርቶችን/ኤክስፖርት እስታንዳርድ ዲዛይኖችን እና ቤንች ማርክ ውጤቶችን/ በዘርፉ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ድጋፉን በተሟላ ሁኔታ የማይሰጥ ከሆነ የገበያ ተፈላጊነትን የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ ለማግኘት በሚታቀደውም ኤክስፖርት ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## የአካባቢ ብክለትን በተመለከተ

157. ኢንስቲትዩቱ በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 መሰረት በካይ ፈሳሽ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያውያን ላይ ጉዳት የሚያደርስ በካይን ለመከላከል የክትትል እና ድጋፍ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

158. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በናሙና የተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች( አዋሽ፣ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ሲሆኑ፡- የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ፋብሪካዎቹ፡-

- ወደ ውሃ አካላትና ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ የፍሳሽ ደረጃዎችን ጠብቀው የሚለቁ ስለመሆኑ፣

- ❖ የአካባቢ አየር ጥራትን የሚገልፁና ለማይንቀሳቀሱ እና ለሚንቀሳቀሱ የአየር ብክለት ምንጮች የተፈቀዱትን የልቀት መጠኖች የሚወስኑ የአየርጥራት ደረጃዎችን ጠብቀው፣
- ❖ እንዲሁም የንፁህ አመራረት ዘዴና የአካባቢ እንክብካቤ መርህን ተከትለው እያመረቱ ስለመሆናቸው ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

1. አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ፡- የአካባቢ ጥበቃ ህጎችንና ደንቦችን ጠብቀው ለመሥራት የሁለተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ በመገንባት ላይ ያለ መሆኑ፣
2. ባቱ ቆዳ ፋብሪካ፡- የሚለቀቁ ፍሳሾችን በተመለከተ በአገሪቱ እስታንዳርድ መሰረት ወደ ውሃ አካላት የሚለቁ መሆኑን ሲገልፁ የአየር ጥራት ደረጃዎችን እስካሁን ያልተገበሩ ሲሆን፤ የንፁህ አመራረት ዘዴን በተመለከተ በፕሮጀክት ደረጃ እያከናወኑ መሆኑን፣
3. ብሉናይል ቆዳ ፋብሪካ፡- በኦዲቱ ወቅት ሥራ አቁሞ የተገኘ መሆኑ፣
4. ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፡- ከምርት የሚለቀቀውን ፍሳሽ በ 2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ አጣርቶ ወደ ውሃ አካላት የሚለቅ ሲሆን፤ የንፁህ አመራረት ዘዴ እና የአካባቢ እንክብካቤ መርህን ተከትሎ የሚያመርት መሆኑ፣
5. ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ፡- ፋብሪካው እስከ 3ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ መገንባት የሚጠበቅበት በመሆኑ ጥረት በማድረግ ላይ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በአንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ እያመረተ መሆኑ፣
6. ሞጆ ቆዳ ፋብሪካ፡- ፋብሪካው በአሁኑ ወቅት በአንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ሙሉ ለሙሉ እያጣራ ሲሆን የ2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያን 50% እየተጠቀመ መሆኑ፣
7. ገላን ቆዳ ፋብሪካ፡- በአሁኑ ወቅት አንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ እየተጠቀመ መሆኑ፣
8. ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ፡- የ2ኛ ደረጃ ማጣሪያ ያለው ሲሆን፤ ክሮምን እንደገና በመጠቀም ለአገልግሎት የሚያውል መሆኑ፣
9. ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ፡- አንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ያለው መሆኑ፣ በሥራ ኃላፊዎቹ በኦዲቱ ወቅት በተሰጠ መልስ ታውቋል፡፡

159. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ በሞጆ እና በባህርዳር ከተሞች በመስክ በመገኘት የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የቆዳ ፋብሪካዎቹ የሚጠበቅባቸውን የአካባቢ እንክብካቤ አክብረው የሚሰሩ ስለመሆኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ የሞጆ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ፣ደን እና አየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን የሥራ ኃላፊ በሰጡት መልስ በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡት(ሞጆ፣ኮልባ እና ገላን) በሞጆ ከተማ መስተዳድር ስር ሲሆኑ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን በነሱ ስር አለመሆኑን ገልፀው እነሱ የሚከታተሏቸው ሶስቱም ፋብሪካዎች በአዋጁ መሰረት ከፋብሪካዎቻቸው የሚለቀቁ ፍሳሾችን ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ የማይለቁ ሲሆን፤ ያላቸውም የፍሳሽ ማጣሪያ ያልተሟላ በመሆኑ ምክንያት ከፋብሪካዎቹ የሚወጣው በካይ

ፈሳሽ አፈር፣ውሃና አየርን የሚበክል መሆኑ የታወቀ መሆኑን ገልፀው፤ የአየር ጥራትን በተመለከተ ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል አሰራር እስካሁን የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

160. እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለባህርዳር የአካባቢ ጥበቃ ደን እና ዱር እንስሳት ባለስልጣን የሥራ ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ፋብሪካዎቹም ሆነ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤቱ የፍሳሽ ደረጃን የሚፈትሹበት ላቦራቶሪ የሌለ መሆኑን በመግለፅ መልስ የሰጡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

161. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ የኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከ 2008- 2010 ዓ.ም የፍሳሽ ናሙናዎችን በመሰብሰብ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ከመረጣቸው 9 ፋብሪካዎች( አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) አምስት የቆዳ ፋብሪካዎች( አዋሽ፣ ባቱ፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ እና ሞጆ) ቆዳ ፋብሪካዎች በኢንስቲትዩቱ ላቦራቶሪ የተመረመሩ መሆናቸውን ሲገልፁ የቀሩት ሶስት ፋብሪካዎች(ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) በፍተሻው ውስጥ ስለመካተታቸው መልስ ያልሰጡ ሲሆን፤ ብሉናይል ቆዳ ፋብሪካ በኦዲቱ ወቅት ሥራ ማቆሙ ታውቋል፡፡

162. እንዲሁም የአየር ጥራትን በተመለከተ የኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳሬክተር በሰጡት መልስ ከቆዳ ፋብሪካዎች የሚፈጠሩትን የአየር በካዮች ለመቀነስ የሚቻለው ፋብሪካዎች የፍሳሽ ማጣሪያቸውን በአግባቡ ሲጠቀሙና የንፁህ አመራረት ቴክኖሎጂን ሲጠቀሙ መሆኑን ገልፀው ለዚህም በኢንስቲትዩቱ ስልጠና መሰጠቱን ገልፀዋል፡፡

163. በተጨማሪም በኢንስቲትዩቱ የኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት በአገሪቱ በዘርፉ ባሉ ቆዳ ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝን በተመለከተ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የቆዳ ፋብሪካዎች የፍሳሽ፣ የደረቅ እና ወደ አየር የሚለቀቁ በካዮችን በኢትዮጵያ የወጣውን ደረጃ እንዲያሟሉ የምክር አገልግሎት መስጠት ሲሆን የፍሳሽ ማጣሪያን በሚመለከት የፍሳሽ ቆሻሻ ከሚፈጠርበት ከእያንዳንዱ የማምረት ሂደት መስመር ተለይቶ የሚወጣበትን እና ወደ ማጣሪያ ጣቢያ ከመግባቱ በፊት ጠጣር የሆኑ ነገሮች የሚለዩበትን እንዲሁም ለየብቻ የተለዩ ፍሳሾች ለየብቻቸው በሚጠራቀሙበት ማጠራቀሚያ ውስጥ በአግባቡ ከታከሙ በኋላ ወደ ሚቀላቀሉበት ገንዳ ገብተው በኬሚካል የሚታከሙበትን ይህንንም ሂደት ሲጨርሱ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ማጣሪያ ገብተው በመጀመሪያው ደረጃ ያልተጣሩት በሁለተኛው ደረጃ የሚጣሩበትን ስርዓት እንዲከተሉ በዚህም ሂደት በየቀኑ የሚጨመሩ ኬሚካሎች በአግባቡ መጨመራቸውን፤በአግባቡ በአየር መቃጠል ያለባቸው በተገቢው መንገድ አየር እንዲያገኙ መደረጉን፤ እንዲሁም በሂደቱ የሚፈጠሩት ደረቅ ቆሻሻዎች በአግባቡ መሰብሰባቸውን ክትትል እንዲያደርጉ በመጨረሻ የሚወጣው ፍሳሽ ከኢትዮጵያ የቆዳ ፋብሪካዎች ፍሳሽ

ልቀት ደረጃ ጋር ለማወዳደር እንዲቻል በላቦራቶሪ እንዲያስመረምሩ እና በመረጃ እንዲይዙ የማድረግ ሥራ የሚሰራ መሆኑ በዳይሬክተር ተገልጿል፡፡

164. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡት 9 ቆዳ ፋብሪካዎች ሶስቱ (ባቱ፣ ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና ባህርዳር) በ 2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ የሚሰሩ ሲሆን 6ቱ በአንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው በስድስቱ ፋብሪካዎች በኩል የአካባቢ ብክለትን ማስወገድ የማይቻል መሆኑ ሲታወቅ ፤ የሁለተኛ ደረጃ ያላቸውም ቢሆን በላቦራቶሪ ተደግፈው መሥራት ያለባቸው ሲሆን፤ በመጨረሻም እያንዳንዳቸው ሶስተኛ ደረጃ ፍሳሽ ማጣሪያ ገንብተው መሥራት ያለባቸው መሆኑን የአሰራር ስርዓቱ ያመለክታል፡፡

165. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2ኛ ደረጃ ማጣሪያ ኖሯቸው በላቦራቶሪ ተደግፈው እንዲሰሩ እና ወደ ሶስተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ እንዲሸጋገሩ ቀጣይነት ያለው ምክር ካልሰጠ ፋብሪካዎቹ አሁን ባሉበት አንደኛ ደረጃ የሚቀጥሉ ከሆነ በፍሳሽ ብክለት ምክንያት በአካባቢያቸው እና በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ይሆናል፡፡

166. 

በሞጆ የሚገኘው የገላን ቆዳ ፋብሪካ አንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ፎቶግራፍ




በባህርዳር የሚገኘው የሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ አንደኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ፎቶግራፍ

## የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ

167. ኢንስቲትዩቱ የህብረተሰብን ጤና የማይጎዱ ለአካባቢ የተስማሙ የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻን አያያዝ ያሚሉ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች እንዲኖሩ የቴክኒክና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

168. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በናሙና የተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች(አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ የኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ሞጆ፣ ገላን፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ሲሆኑ፡- በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ ፋብሪካ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጡ መልሶች፡- (አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኮልባ፣ ሞጆ፣ ገላን እና ሀበሻ) ቆዳ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ ስልጠና የሰጣቸው መሆኑን ቢገልፁም፤ስልጠና ስለመውሰዳቸው የሚያመለክት ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ ሲታወቅ፤ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር እና ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካዎች ስልጠና የወሰዱ ሰራተኞች ስም ዝርዝር ማስረጃ በማቅረብ የስልጠና ድጋፍ የተሰጠ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

169. ኢንስቲትዩቱ የረቂቅ ሪፖርት በቀረበለት ወቅት የፍሳሽ ማጣሪያ ዘዴን በተመለከተ ከአዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉ ናይል፣ ገላን፣ ሞጆ እና ኢትዮጵያ ቆዳ አ.ማ ቆዳ ፋብሪካች ለመጡ ሰራተኞች ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚያመለክት አቴንዳንስ (የመቆጣጠሪያ ሰነድ) አቅርቦ በኦዲት ቡድኑ ታይቷል፡፡

170. የኦዲት ቡድኑ በናሙና የተመረጡ ቆዳ ፋብሪካዎች(ኮልባ፣ ሞጆ እና ገላን) የቴክኒክና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ከኢንስቲትዩቱ በማግኘት የህብረተሰብን ጤና በማይጎዳ እና ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መልኩ የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻን አያያዝ ስርዓትን በማሟላት ሥራቸውን እየሰሩ ስለመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለሞጆ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ፣ደን እና አየር ንብረት ለውጥ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ፡- ኮልባ፣ሞጆ እና ገላን ቆዳ ፋብሪካዎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ በዘርፍ በዘርፉ ሳይለዩ በማቀላቀል ወደ አካባቢ የሚያስወግዱ ሲሆን፤ ፍሳሽን በተመለከተ የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓትን ባሟላ መልኩ ተከትለው የማይሰሩ በመሆኑ የአካባቢ ብክለት በማድረሳቸው የፋብሪካ ባለንብረቶችና ማናጀሮች በተገኙበት እየደረሰ ባለው ብክለት ዙሪያ እና ወደፊት መደረግ ባለበት ጉዳይ ላይ የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣኖች እና የሞጆ ከንቲባ በተገኙበት ውይይት እና ምክክር መደረጉን ገልፀው የችግሩን አሳሳቢነት የሚያመለክት ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

171. እንዲሁም ፋብሪካዎቹ በአካባቢ ላይ ያደረሱት ጉዳት በቀንድ ከብቶች ላይ የቆዳ መላላጥ፣ መክሳት እና ለሞት መዳረግ ሲሆኑ፤ ከወንዝ አሸዋ በሚያወጡ ሰዎች ላይ ሰውነት የማቁሰል፤ የማሳከክና የመሳሰሉት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

172. በተጨማሪም በመስኖ በሚመረቱ ሰብሎች ላይ የማቀጨጭ፣ ማቃጠልና ምርት መቀነስ ሲሆኑ፤ በውሃ አካል ውስጥ በሚኖሩ እንስሳት ላይ በተለይም የዓሳ ዝርያዎችን ማጥፋትና ዝርያቸውን መቀነስ እና ከፋብሪካዎቹ በሚወጡ መጥፎ ሽታዎች ምክንያት የአካባቢው ኗሪዎች በአስም እና ሳይነስ በሽታ እየተጠቁ መሆኑን ያሳወቁ ሲሆን ፋብሪካዎቹም ለፈጠሩት ችግር ማስጠንቀቂያ በደብዳቤ ቁጥር ATENBJQ/198/2010 በቀን 20/10/2010 ዓ.ም የተፃፉ ለሞጆ እና ለኮልባ ቆዳ ፋብሪካዎች እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

173. ለባህርዳር የአካባቢ ጥበቃ ደን እና ዱር እንስሳት ባለስልጣን የሥራ ኃላፊ ባህርዳር እና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ ሁለተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ የገነባ ቢሆንም፤ ከዚህ ፍሳሽ ማጣሪያ የሚወጣውን ዝቃጭ ማጣሪያው የማጣራት ብቃት ስለሚያንሰው በቀጥታ ወደ ዓባይ ወንዝ የሚለቅበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀው ፋብሪካው ክሮምን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል/Recovery/ ሥራ የሚጠቀም በመሆኑ ብክለቱ ዝቅተኛ ነው ተብሎ ቢገመትም የመጨረሻ የፍሳሽ ልቀቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የማይረጋገጥ በመሆኑ የፍሳሽ ደረጃውን የጠበቀ ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን አሳውቀው፤ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ በሁለቱም ቆዳ ፋብሪካዎች በባህርዳር እና ሀበሻ ደረቅ ቆሻሻ ለያይቶ የማስወገድ ሥራ የማይሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

174. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ ኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ አብዛኛዎቹ የቆዳ ፋብሪካዎች የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ያላቸው በመሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ማጣሪያ እንዲገነቡ ለውጭ አማካሪ መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችን በመስጠት የሚሰሩበትን ጊዜያት የጊዜ ሰሌዳ የማውጣት እና የቴክኒክ ድጋፍ የሰጡ መሆኑን እና በዚሁም መሰረት በፍሳሽ ማጣሪያ ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች ስልጠና በመስጠት የእያንዳንዱን ቆዳ ፋብሪካ የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታ ክትትል የማድረግ ሥራዎች ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን ቢገልፁም የተደረገውን ክትትል የሚያመለክት ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

175. ኢንስቲትዩቱ የስልጠና ድጋፍ ተሰጥቷል ቢልም በእቅድ የታገዘ ወቅታዊ የክትትል ሥራ ያልሰራ በመሆኑ ፋብሪካዎቹ ፍሳሻቸውን በጥንቃቄ ባለመልቀቃቸው አካባቢን ከመበከል ያልተቆጠቡ መሆኑን እና የንፁህ አመራረት ዘዴን በመጠቀም ደረቅ ቆሻሻን የመለየት ሥራ በመሥራት የማያስወግዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በተሰጡ መልሶች የኦዲት ቡድኑ ሊገነዘብ ችሏል፡፡

176. ኢንስቲትዩቱ የሚሰጣቸውን የአካባቢ እንክብካቤ አያያዝ ስልጠናዎች መተግበራቸውን በእቅድ በመመራት ወቅታዊ ክትትል ካላደረገ ፋብሪካዎች አካባቢን በመበከል የሚቀጥሉ ሲሆን ህብረተሰብም ፋብሪካዎቹን በሚያደርሱት ጉዳት ምክንያት ሥራቸውን ወደ ማስቆም ደረጃ ይደርሳል፡፡

## የፍሳሽ ናሙና ምርመራን በተመለከተ

177. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የፍሳሽ ናሙና እንዲያስመረምሩ እና የልቀት ደረጃቸውን እንዲያውቁ ሊደግፍ ይገባል፡፡

178. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 9 የቆዳ ፋብሪካዎች 3ቱ (ብሉናይል፣ ኮልባ፣ ገላን፣) የፍሳሽ ናሙ.ያ ያላስመረመሩ መሆኑን ታውቋል፡፡

179. ስለሁኔታው በኢንስቲትዩቱ ኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በናሙና ከተመረጡት ቆዳ ፋብሪካዎች ለአዋሽ እና ኢትዮጵያ ቆዳ አክስዮን ማህበር በመስክ ክትትል የሰሩትን የላቦራቶሪ ፍተሻ በማየት የምክር አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ሲገልፁ የቀሩትን 7 የቆዳ ፋብሪካዎች በተመለከተ መልስ ያልሰጡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

180. ኢንስቲትዩቱ ላቦራቶሪ እና ባለሙያ ለሌላቸው ፋብሪካዎች ላቦራቶሪ እንዲኖራቸው የምክር አገልግሎቱን በመስጠት አሁን ባሉበት ደረጃ በተከታታይ የፍሳሽ ናሙና ወስዶ በመመርመር

ያለበትን ደረጃ በማሳወቅ የሚጠበቀውን የተጣራ ፍሳሽ ፋብሪካዎቹ ወደ ውሃ አካላት የሚለቁበት ደረጃ መድረሳቸውን ካልተከታተለ የሚለቀቀው የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ፍሳሽ የብክለት መጠን በመጨመር በውሃ ውስጥ ባሉ እንስሳት፣ በከብቶች እና በሰው ጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት አሳሳቢ ደረጃ የሚያደርስ ይሆናል፡፡

## የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራዎችን በተመለከተ

181. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ እቅድ፣ የአካባቢ አያያዝ ፕሮፋይል፣ የፍሳሽ ማጣሪያ እና የልቀት ደረጃ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ እንዲሰሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
182. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ ኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ አጠቃላይ የአካባቢ ደሰሳ ጥናት በማጥናት የቆዳ ፋብሪካዎቹ ያላቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን በመለየት የፋብሪካ ባለቤቶች እና ሥራ አስኪያጆች በተገኙበት መስተካከል የሚገባቸው እንዲስተካከሉ ተደርጓል ከሚል ውጪ ስለመረጃ እና ማስረጃ አሰባሰብ የተሰጠ የምክር አገልግሎት የመስክ ክትትል ማስረጃን በማቅረብ የሰጡት መልስ አለመኖሩ በኦዲቱ ታውቋል፡፡
183. በነባራዊ ሁኔታ ላይ በኢንስቲትዩቱ የተሰጠ መልስ ለቆዳ ፋብሪካዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የዘወትር ተግባር መሆኑ ተገልፆ እያንዳንዱ ፋብሪካ የደረሰበትን የአካባቢ አያያዝ ደረጃ የሚያሳይ መረጃ ተያይዞ ቀርቧል የሚል ቢሆንም፣ በኦዲቱ መሰረት የቀረበው ጥያቄ ፋብሪካዎቹ የማስረጃ አያያዝ ስርዓት እንዲኖራቸው በመስክ ክትትል የምክር አገልግሎት እንደሰጡ ስለመደረጉ መልስ እንዲሰጥ የተፈለገ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ባደረጋቸው ምልከታ ችግር መኖሩን ካረጋገጠበት አኳያ በኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡
184. ኢንስቲትዩቱ ፋብሪካዎቹን መደገፍ በሚገባው የአካባቢ አያያዝ እቅድ፣ የአካባቢ አያያዝ ፕሮፋይል፣ የፍሳሽ ማጣሪያ እና የልቀት ደረጃ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ ድጋፍ ካልሰጠ በፋብሪካዎች የሚሰሩ ሥራዎች በማስረጃ ላይ ያልተደገፉ ከማድረጉም በላይ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጉታል፡፡

## የኢንዱስትሪዎችን እድገት ለማፋጠን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ

185. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎችን ዕድገት ለማፋጠን ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ሊሰራ፣ ሥራዎችን ሊከታተል፣ሊገመግምና ለሚከሰቱ ችግሮች በጋራ ውይይት መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል፡፡

186. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት የተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- ኢንስቲትዩቱ በቆዳው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች በተለያዩ መድረኮች ለሚያነሷቸው ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ላይ የቅንጅታዊ አሰራር ውስንነት የሚታይበት መሆኑ ከ 2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡

187. ስለሁኔታው የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች/ማኔጅመንት/ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ባለሀብቶች በተለያዩ መድረኮች የሚያነሷቸውን ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት( ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ እንዲሁም ከሌሎች ተቋማት) ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ያለ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት የጋራ እቅድ በማቀድ ሥራዎችን ለመሥራት ጅምር ሥራዎች ያሉ ቢሆንም፤ አፈፃፀሙ ክፈተት የሚታይበት መሆኑን የኢንስቲትቱ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

188. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ኢንስቲትዩቱ በሰጠው መልስ በምርት ግብዓት፣ በፋይናንስ እና በኃይል አቅርቦት እንዲሁም የጉምሩክና ሎጂስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥን ጨምሮ ከሌሎች የንዑስ ዘርፉን የምርትና ኤክስፖርት ሥራ ከሚደግፉ ባለድርሻ አካላት እና የመንግስት ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሥራዎችን በጋራ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ቢሆንም እስካሁን ባለው ሁኔታ በታቀደው ልክ ውጤታማ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

189. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚጠበቀው ደረጃ ተቀናጅቶ ካልሰራ፣ ሥራዎችን በወቅቱ ካልተከታተለ ካልገመገመ እና ለሚከሰቱ ችግሮች በጋራ ውይይት መፍትሄ ካልሰጠ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎችን ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይፋጠን እና ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ

190. ኢንስቲትዩቱ የኤክስፖርት ቆዳ እና ቆዳ ውጤቶችን ምርት ለማሳደግ ከኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት( የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር እና የቆዳ አቅራቢዎች ማህበር) ጋር በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

191. ኢንስቲትዩቱ በዚህ መሰረት እየተገበረ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሩክተር ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የንዑስ ዘርፉን ኩባንያዎች(ኢንዱስትሪዎች) ወርሃዊ የኤክስፖርት

አፈፃፀም ጨምሮ ወቅታዊ ኩነቶችንና ሌሎች ጉዳዮችን ለሁሉም ፋብሪካዎች በየጊዜው በኢሜይል እንዲደርሳቸው በማድረግ የመረጃ ልውውጥ የሚያደርግ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ ኢንስቲትዩቱ ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ የዘርፉን አፈፃፀምና ወቅታዊ ጉዳዮች ተደራሽ ለማድረግ ዌብ ሳይትን ጨምሮ ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ተደራሽ የሚያደርግ መሆኑን ገልፀው ከዘርፉ ጠቃሚ መረጃዎች ጋር በተያያዘ በቀድሞው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል ለመረጃ አያያዝና ልውውጥ የሚረዳ የተለየ ዳታቤዝ እንዲዘጋጅ ተወስኖ በሂደት ላይ ያለ ቢሆንም እስካሁን ተጠናቆ ሥራ ላይ ሊውል ያልቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

192. ኢንስቲትዩቱ የዳታ ቤዝ አሰራር ስርዓት ወቅታዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት ካልተገበረ የኤክስፖርት ቆዳ እና ቆዳ ውጤቶችን ምርት ለማሳደግ ከኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት( የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር እና የቆዳ አቅራቢዎች ማህበር) ጋር የሚደርገው የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር አፈፃፀም ቀልጣፋና

ውጤታማነትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ኢንዱስትሪዎች የታዩ ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

193. ኢንስቲትዩቱ ከቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማታዊ ባለሀብት እና ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ጋር መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎች እና ተግባሮች ላይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ በቅንጅት የሚሰራ ቢሆንም ውጤታማ አለመሆኑ፣

194. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ባዘጋጀው ቻርተር መሰረት ድጋፉን ለሚፈልጉ ፋብሪካዎች ያላሳወቀ መሆኑ፣

195. የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ በናሙና ከተመረጡ 5 የቆዳ አልባሳት ለሶስቱ የአዋጭነት ጥናት ያልሰራ መሆኑ ይህም የፋብሪካዎችን ፍላጎት በመጠየቅ የማይሰራ በመሆኑ ክፍተት የሚታይበት መሆኑ፣

196. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ የቴክኒካል ስልጠናና ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች ለ 5ቱ ያልሰጠ መሆኑ፣

197. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ ጫማ ፣የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ኢንዱስትሪዎችን ዘርፍን ልማት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የሥራ አመራር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን አዘጋጅቶ መስጠቱን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች ስልጠና ለ 4ቱ፣ ከ 5 ቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ለአንዱ እና ከቆዳ ፋብሪካዎች ከ 9ኙ 3ቱ ስልጠና ያልወሰዱ ሲሆን ከጫማ ፋብሪካ ስልጠናውን ከወሰዱት አንበሳ ጫማ ፋብሪካ የሚሰጠው ስልጠና በፋብሪካ ደረጃ በመመጣጠን በኩል ችግር እንዳለበት የገለፁ መሆኑ፣

198. ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና የግብዓት ትስስር ድጋፍ የመፍጠር ክፍተት የሚታይበት መሆኑ፣

199. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ስትራቴጂ ጥናቶች ያስጠና ቢሆንም የገበያ ማፈላለግና ትስስር የመፍጠር ችግር የሚታይበት መሆኑ፣

200. ኢንስቲትዩቱ በምርት ናሙና፣ በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የማማከር አገልግሎት በናሙና ለተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች በተሟላ ሁኔታ የምክር አገልግሎት ያላዳረሰ መሆኑ፣

201. ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር የሚሰራ ቢሆንም፤ በጋራ የምርምር ሥራዎችን በማከናወን በቆዳ እና ቆዳ

ውጤቶች ዘርፍ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር በማድረግ በኩል ክፍተት የሚታይበት መሆኑ፣

202. ኢንስቲትዩቱ በበዓላትና በአዘቦት ወቅት የእንስሳት እርድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች የጥሬ ቆዳ ግብዓት በእርድ ወቅት ጥንቃቄ እንዲደረግለት በቆዳ አሰባሰብ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑ፣

203. በእርድ ወቅት የቆዳ ጥራት ተጠብቆ ገፈፋ እንዲካሄድ የቆዳና ሌጦ መግፈፊያ ቴክኖሎጂ በቄራዎች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ቴክኖሎጂው ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ ኢንስቲትዩቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በፈፃሚ አካልነት የተመደበ ቢሆንም፤ ያልተገበረ መሆኑ፣

204. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ለተሰማሩ የኢንዱስትሪ ባለሀብቶች በምርት እቅድና በምርት ማምረት ሂደት እና ጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች ለ 5ቱ እና ከ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች ለ7ቱ አገልግሎቱን ያልሰጡ መሆኑ፣

205. ኢንስቲትዩቱ ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች እስታንዳርዳቸውን ጠብቀው በጥራት የተመረቱ ስለመሆናቸው የላቦራቶሪ ፍተሻ ድጋፍ የሚያደረግ በመሆኑ ከ 8 ጫማ ፋብሪካዎች 7ቱ የፍተሻ አገልግሎት ያገኙ መሆናቸውን ቢገልፁም ከቅርብ ጊዜ ወደህ በክፍያ የሚሰራ በመሆኑ ድጋፍ ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን የገለፁ መሆኑ፣

206. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ እና ቆዳ አልባሳት ከዲዛይን እስከ ማጠናቀቅ የማሽን አገልግሎት እና የባለሙያ እገዛ መስጠቱን በተመለከተ ከ 8 ጫማ ፋብሪካዎች አንዱ የማሽን እገዛ ያላገኘ ሲሆን ሌላኛው የማሽን እና የባለሙያ እገዛ ያልተሰጠው መሆኑ ሲገለፅ ከ 5 ቆዳ አልባሳት ፋብሪካዎች አንዱ የባለሙያ እገዛ ያልተደረገለት ሲሆን ሌላው ሁለቱንም ድጋፍ ያላገኘ መሆኑ፤ በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ለድጋፍ ፈላጊዎች ድጋፍ የማያዳርስ መሆኑ፣

207. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ፣ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች የምርት ማልማት/ኤክስፖርት እስታንዳርድ ዲዛይኖች/ አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ ከ 8 ጫማ ፋብሪካዎች ለ3ቱ እና ከ 5 የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ፋብሪካዎች ለ 4ቱ ያልሰጠ በመሆኑ ድጋፉን ለድጋፍ ፈላጊዎች የማያዳርስ መሆኑ፣

208. ኢንስቲትዩቱ በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 መሰረት በካይ ፈሳሽ፣ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያውያን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በካይን ለመከላከል የክትትል እና ድጋፍ እንዲሁም ስልጠና እየሰጠ ቢሆንም ወቅታዊ ክትትል ላይ ችግር የሚታይበት በመሆኑ የቆዳ ፋብሪካዎች አካባቢን ከመበከል እና በህብረተሰብ ላይ ጤና ጉዳት ከማድረስ ያልተቆጠቡ መሆኑ፣

209. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የፍሳሽ ናሙና እንዲያስመረምሩ እና የልቀት ደረጃቸውን እንዲያውቁ ማድረጉን በተመለከተ ከ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች 3ቱ( ገላን፣ ኮልባ እና ብሉናይል) የላቦራቶሪ ፍተሻ ድጋፍ ይልሰጠ መሆኑ፡፡

210. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ እቅድ፣ የአካባቢ አያያዝ ፕሮፋይል፣ የፍሳሽ ማጣሪያ እና የልቀት ደረጃ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ እንዲሰሩ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣

211. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎችን ዕድገት ለማፋጠን ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ቢሆንም፤ ለሚከሰቱ ችግሮች በጋራ ውይይት መፍትሄ ከመስጠት አኳያ ችግር ያለ መሆኑ፣

212. ኢንስቲትዩቱ በሀገር ውስጥ ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከውጭ ከህንድ ማዕከላዊ ላቦራቶሪ ጋር የትብብር ሥራ እየሰራ ቢሆንም በሀገር ውስጥ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች መካከል የትብብር/ትስስር ሥራ በመሥራት በኩል ክፍተት የሚታይበት መሆኑ፣

213. ኢንስቲትዩቱ የኤክስፖርት ቆዳ እና ቆዳ ውጤቶችን ምርት ለማሳደግ ከኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት( የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር እና የቆዳ አቅራቢዎች ማህበር) ጋር በቅንጅት ለመሥራት በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዳታ ቤዝ ስርዓት ያልተገበረ መሆኑ፣

## የማሻሻያ ሀሳቦች

214. ኢንስቲትዩቱ ከቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማታዊ ባለሀብት እና ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ጋር መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎች እና ተግባሮች ላይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ውጤታማ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

215. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን በቻርተር ላይ የተመለከቱ የድጋፍ አገልግሎቶች ድጋፉን ለሚፈልጉ ፋብሪካዎች ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

216. የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የአዋጭነት ጥናት በማዘጋጀት ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ሁሉ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

217. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ የቴክኒካል ስልጠናና ድጋፍ ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

218. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ ጫማ ፣የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ኢንዱስትሪዎችን ዘርፍን ልማት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የሥራ አመራር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በፋብሪካዎች ደረጃ አዘጋጅቶ ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

219. ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና የግብዓት ትስስር ድጋፍ ሊፈጥር ይገባል፡፡

220. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች ባስጠናው የገበያ ስትራቴጂ ጥናቶች የገበያ ማፈላለግና ትስስር የመፍጠር ችግሮችን ሊፈታበት ይገባል፡፡

221. ኢንስቲትዩቱ በምርት ናሙና፣ በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የማማከር አገልግሎት ለሁሉም አገልግሎት ፈላጊ ፋብሪካዎች ሊያዳርስ ይገባል፡፡

222. ኢንስቲትዩቱ የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ የምርምር ሥራዎችን በማከናወን በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ሊሰራ ይገባል፡፡

223. ኢንስቲትዩቱ በበዓላትና በአዘቦት ወቅት የእንስሳት እርድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች የጥሬ ቆዳ ግብዓት በእርድ ወቅት ጥንቃቄ እንዲደረግለት በቆዳ አሰባሰብ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

224. በእርድ ወቅት የቆዳ ጥራት ተጠብቆ ገፈፋ እንዲካሄድ የቆዳና ሌጦ መግፈፊያ ቴክኖሎጂ በቄራዎች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ቴክኖሎጂው ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ ኢንስቲትዩቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

225. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ለተሰማሩ የኢንዱስትሪ ባለሀብቶች በምርት እቅድና በምርት ማምረት ሂደት እና ጥራት ቁጥጥር ላይ የማማከር አገልግሎት ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊ ፋብሪካዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

226. ኢንስቲትዩቱ ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች እስታንዳርዳቸውን ጠብቀው በጥራት የተመረቱ ስለመሆናቸው የላቦራቶሪ ፍተሻ ድጋፉን ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊ አገልግሎት መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ከክፍያ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ለተጠቃሚዎቹ በግልፅ ሊያስረዳና ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

227. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ እና ቆዳ አልባሳት ከዲዛይን እስከ ማጠናቀቅ የማሽን አገልግሎት እና የባለሙያ እገዛ ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊዎች ሊያዳርስ ይገባል፡፡

228. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ፣ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች የምርት ማልማት/ኤክስፖርት እስታንዳርድ ዲዛይኖች/ አገልግሎት ለሁሉም ድጋፍ ፈላጊዎች ሊያዳርስ ይገባል፡፡

229. ኢንስቲትዩቱ በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 መሰረት በካይ ፈሳሽ፣ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያውያን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በካይን ለመከላከል የሰጠው ስልጠና ተግባራዊ ስለመሆኑ ወቅታዊ ክትትል በማድረግ የቆዳ ፋብሪካዎች አካባቢን በመበከል እና በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የማማከር ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፣፡

230. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የፍሳሽ ናሙና እንዲያስመረምሩ እና የልቀት ደረጃቸውን እንዲያውቁ ለሁሉም ፋብሪካዎች በናሙና ምርመራ ደረጃቸውን ሊያሳውቅ ይገባል፡፡


231. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ እቅድ፣ የአካባቢ አያያዝ ፕሮፋይል፣ የፍሳሽ ማጣሪያ እና የልቀት ደረጃ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ እንዲሰሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

232. ኢንስቲትዩቱ የኤክስፖርት ቆዳ እና ቆዳ ውጤቶችን ምርት ለማሳደግ ከኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት( የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር እና የቆዳ አቅራቢዎች ማህበር) ጋር በቅንጅት ለመሥራት በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዳታ ቤዝ ስርዓት ሊተገብርይገባል፡፡

## አባሪዎች ብዛት 4

**አባሪ 1**

### የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መዋቅር



አባሪ 2

**ኦዲት ተደራጊው መ/ቤቱ፡-** የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

**የኦዲት አከባቢ** (Potential Audit Area) ፦ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር አፈጻጸም

ቀልጣፋና ውጤታማነትን መገምገም፡፡

| **የኦዲቱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች** /Audit main Issues/ | **የመመዘኛ መስፈርት** /Evaluative Criteria/ | |
|---|---|---|
| 1. ኢንስቲትዩቱ የቆዳና የቆዳ ውጤቶችን ፣ ኢንዱስትሪዎችን ለማሳደግ ፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የአሰራር ስርአቶችን የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡ | 1. ኢንስቲትዩቱ ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ሊያዘጋጅ እና ሲፈቀድም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ /ምንጭ፡- የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 2/ | |
| | 2. ኢንስቲትዩቱ የቆዳና የቆዳ ፣ ውጤቶች (ጫማ፣ጓንት፣የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች) ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን አዘጋጅቶ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡<br><br>/ምንጭ፡- የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3 | |
| | 3. ኢንስቲትዩቱ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የአዋጭነት | |

| | | |
|---|---|---|
| | ጥናት በማዘጋጀት ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡<br><br>/**ምንጭ**፡-የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3 | |
| 2. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ ማኒፋክቸሪንግን ልማትን ለማጠናከር የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ፣ የአቅም ግንባታ፣ የግብዓት ፣ የገበያ ማስተዋወቅና ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የድጋፍና ክትትል አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣ | 4. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የምክር እና ቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br><br>/**ምንጭ**፡- የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3/ | |
| | 5. ኢንስቲትዩቱ በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡<br><br>**ምንጭ**፡- የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3/ | |
| | 6. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በግንባታ፣ በመሳሪያ ተከላና በምርት ሙከራ /ኮሚሽኒንግ/ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br><br>**ምንጭ**፡- የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181 /2002 ገጽ 3 እና የተገልጋዮች ቻርተር ገፅ 6/ | |
| | 7. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ባለሀብቶች አነስተኛ ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ የቴክኒካል፣ ስልጠና ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ /የተገልጋዮች ቻርተር ገፅ 7/) | |
| | 8. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን የድጋፍ አገልግሎቶች በግልፅ ሊያሳውቅና አገልግሎቱን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (የ2009 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ከገፅ 13-15) | |
| | 9. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ፣ጫማ፣ጓንት፣የቆዳ አልባሳት እና ዕቃዎች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና እና ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ሊያዘጋጅ እና ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፣ (ምንጭ፡- ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3) | |
| | 10. ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርትና የግብዓት ትስስር ሊፈጥር ይገባል ፣ (ምንጭ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተገልጋዎች ቻርተር ገጽ 5) | |
| | 11. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች(ጫማ፣ጓንት፣የቆዳ አልባሳት እና | |

| | | |
|---|---|---|
| | ዕቃዎች) ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶች ሊያከናውን፤እንዲሁም የገበያ ማፈላለግና ትስስር ሊፈጥር ይገባል ፤(ምንጭ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3) | |
| | 12. ኢንስቲትዩቱ በምርት ናሙና፣በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች የማማከር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ /የተገልጋዮች ቻርተር ገፅ 7/ | |
| | 13. ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ሊሰራ፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ሊያከናውን፤ እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር ሊያግዝ ይገባል፣ (ምንጭ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3) | |
| | 14. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የኤክስፖርት አፈፃፀምን ለማሳደግ የማኔጅመንት እና የቴክኖሎጂ አቅምን የመገንባትና የማጠናከር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ /የኢንስቲትዩቱ 2009 በጀት ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 23/ | |
| | 15. ኢንስቲትዩቱ በበዓላትና በአዘቦት ወቅት የእንስሳት እርድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማስተዋወቅ | |

| | | |
|---|---|---|
| | (ፕሮሞሽን) ሥራ ሊሰራ እና በአሰባሰብ ሂደትም የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት፣ አያያዝና ግብይት ዙሪያ የሚስተዋሉ ማንቆዎች ለመፍታት የተዘጋጀ የድርጊት መርሀ ግብር ከገፅ 5- 10) | |
| | 16. ኢንስቲትዩቱ ሰፋፊ የእንስሳት እርድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ለአራጆች ስልጠና ሊሰጥና ማንኛውም እርድ ሰርተፊኬት ባላቸው አራጆች ብቻ እንዲከናወን ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት፣ አያያዝና ግብይት ዙሪያ የሚስተዋሉ ማንቆዎች ለመፍታት የተዘጋጀ የድርጊት መርሀ ግብር ከገፅ 5-10) | |
| | 17. ኢንስቲትዩቱ በቄራዎች ውስጥ የቆዳና ሌጦ ጥራት ተቆጣጣሪዎች መኖናቸውን ክትትል በማድረግ የቴክኒክ ክህሎት ማሳደጊያ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት፣ አያያዝና ግብይት ዙሪያ የሚስተዋሉ ማንቆዎች ለመፍታት የተዘጋጀ የድርጊት መርሀ ግብር ገፅ 6) | |
| 3. ኢንስቲትዩቱ ቆዳና የቆዳ ውጤቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ አሟልተው | 18. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና በቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ለተሰማሩ የኢንዱስትሪ ባለሀብቶች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ የድጋፍና የማማከር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፣(ምንጭ ደንብ | |

| | | |
|---|---|---|
| ስለማምረታቸው የሚያረጋግጥ መሆኑን መገምገም፡፡ | ቁጥር181/2002 ገጽ 3) | |
| | 19. ኢንስቲትዩቱ ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች አስታንዳርዳቸውን ጠብቀው በጥራት የተመረቱ ስለመሆናቸው በላቦራቶሪ ፍተሻ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡/የተገል.ጋዮች ቻርተር ገፅ 6/ | |
| | 20. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት ከነከራ እስከ አለቀለት ቆዳ የማሽን አገልግሎት እና የባለሙያ እገዛ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡/የተገል.ጋዮች ቻርተር ገፅ 9/ | |
| | 21. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ፣ በቆዳና የቆዳ አልባሳት ከዲዛይን እስከ ማጠናቀቅ የማሽን አገልግሎት እና የባለሙያ እገዛ ሊሰጥ ይገባል፡፡/የተገል.ጋዮች ቻርተር ገፅ 9/ | |
| | 22. ኢንስቲትዩቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት በጫማ፣በቆዳ፣ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች የምርት ማልማት/ኤክስፖርት ስታንዳርድ ዲዛይኖች/ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡/የተገል.ጋዮች ቻርተር ገፅ 9/ | |
| | 23. ኢንስቲትዩቱ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ወደ ቆዳ ፋብሪካዎች ከመላኩ በፊት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ያወጣውን የጥራት ደረጃ መስፈርት ስለማሟላታቸው በግብይት ማዕከል በተመደበ የጥራት | |

| | | |
|---|---|---|
| | ተቆጣጣሪ ስለመረጋገጡ የፋብሪካ ባለንብረቶች ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ የምክር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፤ (ምንጭ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 005/2007 ዓ.ም) | |
| | 24. ኢንስቲትዩቱ በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 ክፍል መሰረት በካይ ፈሳሽ ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ ወይም በሰው ጤና ወይም በሌሎች ህያውያን ላይ ጉዳት የሚያደርስን በካይን ለመከላከል የክትትልና ድጋፍ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ <br><br> /የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995/ | |
| | 25. ኢንስቲትዩቱ የህብረተሰብን ጤና የማይጎዱ ለአካባቢ የተስማሙ የፈሳሽ እና የደረቅ ቆሻሻን አያያዝ ያሟሉ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች እንደኖሩ የቴክኒክና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ /ከ 2009 በጀት ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 6/ | |
| | 26. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና በቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የፕሮጀክት ዶክመንት ሲያቀርቡ የአከባቢ ተፅኖ ግምገማ ጥናት በስታንደርድ መሰረት መከናወኑን ሊገመግም ይገባል (ምንጭ፡ - የተገልጋዎች ቻርተር ገጽ 4) | |

| | | |
|---|---|---|
| | 27. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የፍሳሽ ናሙና እንዲያስመረምሩ እና የልቀት ደረጃቸውን እንዲያውቁ ሊደግፍ ይገባል፡፡/ከኢንስቲትዩቱ ውጤት ተኮር ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ/ | |
| | 28. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ እቅድ፣ የአካባቢ አያያዝ ፕሮፋይል፣የፍሳሽ ማጣሪያና የቆሻሻ ማስወገጃ የተለያዩ የቴክኖሎጂዎች እና የልቀት ደረጃ መረጃዎችን ማሰባሰብ ሥራ እንዲሰሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡/ከኢንስቲትዩቱ ውጤት ተኮር ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ/ | |
| | 29. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች አምራች የፋብሪካ ባለቤቶች በአስተዳደር ፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ Leather Garment, Goods and Glove Factories Management and Technology Gaps assessment and Analyses ከገፅ 4- 16) | |
| 4. ኢንስቲትዩቱ በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ሀገሪቷ ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ወደምታገኝበት ደረጃ እንድትደርስ እና ወደ ውጭ የሚላክ የምርት | 30. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ኢንደስትሪዎችን ዕድገት ለማፋጠን ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ሊሰራ፣ ሥራዎችን ሊከታተል፣ ሊገመግምና ለሚከሰቱ ችግሮች በጋራ ውይይት መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| መጠን እንዲያድግ ከፋብሪካ ባለንብረቶች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን መገምገም፡፡ | /ከኢንስቲትዩቱ ውጤት ተኮር ዕቅድ እና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ/ | |
| | 31. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች አምራችነት ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ሊያደርግ እና በግል ተቋሟት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ሊያበረታታ ይገባል፡፡ /ምንጭ፡- ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር181/2002 ገጽ 3/ | |
| | 32. ኢንስቲትዩቱ ከቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማታዊ ባለሀብት እና ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ጋር መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች ፣ ደንቦች፣ ዕቅዶች፣መመሪያዎች እና ተግባሮች ላይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ (ምንጭ የ2009 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ገፅ 15) | |
| | 33. ኢንስቲትዩቱ የኤክስፖርት የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶችን ምርት ለማሳደግ ከቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንኡስ ዘርፍ በባለሀብቶች እና ባለድርሻ(የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር፣የቆዳ አቅራቢዎች ማህበር እና ከቆዳ | |

| | | |
|---|---|---|
| | አቅራቢዎች አካላት ጋር በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ (ምንጭ፡የ2008 ፣የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ ከገፅ 25 -27) | |

**አባሪ 3**

**<u>ለኦዲቱ ናሙና ምርጫ በመመዘኛነት ጥቅም ላይ የዋለ እቅድ-አፈፃፀም</u>**

**<u>በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ ጫማ፣ ቆዳ አልባሳት እና ቆዳ ፋብሪካዎች</u>**

<u>ጫማ ፋብሪካዎች የኤክስፖርት እቅድ አፈፃፀም(በሺህ የአሜሪካን ዶላር)</u>

| ተ.ቁ | የፋብሪካው ስም | 2008 በጀት ዓመት | | | 2009 በጀት ዓመት | | | 2010 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አንበሳ ጫማ ፋብሪካ | 4121.74 | 195.21 | 4.74 | 5842.38 | 91.8 | 1.57 | 5929.28 | 373.31 | 6.30 |
| 2. | ጥቁር ዓባይ | 4121.74 | 513.90 | 12.47 | 5265.28 | 1359.3 | 25.82 | 5244.82 | 949.81 | 18.11 |
| 3. | ፒኮክ | 2355.28 | 453.20 | 19.24 | 5277.85 | 253.85 | 4.81 | 4259.73 | 293.11 | 6.88 |
| 4. | ካንጋሮ | 824.35 | 0 | - | 496.36 | 0 | - | 588.70 | 42.41 | 7.20 |
| 5. | ኦኬ ጃማይካ | 471.06 | 4.13 | 0.88 | 799.61 | 24.77 | 3.10 | 948.37 | 60.88 | 6.42 |
| 6. | ኒው ዊንግ አዲስ | 7065.84 | 3662.37 | 51.83 | 12603.80 | 5215.09 | 41.38 | 14948.58 | 4473.96 | 29.93 |
| 7. | ፎንታኒና | 2000.00 | 155.58 | 7.78 | 1940.68 | 48.57 | 2.50 | 2301.71 | 0.47 | 0.02 |
| 8. | ሞደርን ዘጌ | 418.06 | 1.57 | 0.38 | 709.65 | 19.77 | 2.79 | 841.67 | 6.23 | 0.74 |

## የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች የኤክስፖርት እቅድ አፈፃፀም(በሺህ የአሜሪካን ዶላር)

| ተ.ቁ | የፋብሪካው ስም | 2008 በጀት ዓመት | | | 2009 በጀት ዓመት | | | 2010 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ |
| 1. | እንጦጦ ቤተ-ዕደ ጥበብ | - | - | - | 484.49 | 349.11 | 72.06 | 595.24 | 16.24 | 2.73 |
| 2. | ችባን ትሬዲንግ | - | - | - | 75.00 | 132.97 | 177.29 | 595.24 | 243.47 | 40.90 |
| 3. | ያምሮት ገ/መስቀል | - | - | - | 625.00 | 587.93 | 94.07 | 967.26 | 414.45 | 42.85 |
| 4. | የዚችዓለም መዓዛ | 89.08 | 50.98 | 57.23 | 186.52 | 50.67 | 27.17 | 372.02 | 50.71 | 13.63 |
| 5. | ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች | - | - | - | 74.44 | - | - | 74.40 | 5.47 | 7.36 |

## የቆዳ ፋብሪካዎች የኤክስፖርት እቅድ አፈፃፀም(በሺህ የአሜሪካን ዶላር)

| ተ.ቁ | የፋብሪካው ስም | 2008 በጀት ዓመት | | | 2009 በጀት ዓመት | | | 2010 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | እቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ |
| 1. | አዋሽ | - | - | - | | | | | | |
| 2. | ባቱ | 3375.81 | 1082.72 | 32.07 | 3259.31 | 494.02 | 15.16 | 3600.00 | 418.90 | 11.64 |
| 3. | ብሉናይል | 356.37 | 88.20 | 24.75 | 3259.31 | 494.02 | 15.16 | 759 | - | - |
| 4. | ኢትዮጵያ | 11403.88 | 8231.81 | 72.18 | 13656.77 | 8689.64 | 63.63 | 18081.87 | 9471.56 | 52.38 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቆዳ<br>አክስዮን<br>ማህበር | | | | | | | | | |
| 5. | ኮልባ | 8077.75 | 6015.64 | 74.47 | 10441.65 | 5221.45 | 50.01 | 10000.00 | 3351.19 | 33.51 |
| 6. | ሞጆ | 5751.62 | 3998.36 | 69.52 | 7604.81 | 2319.15 | 30.50 | 7000.00 | 931.56 | 13.31 |
| 7. | ገላን | 1850.97 | 551.31 | 29.78 | 848.58 | 215.08 | 23.35 | 713.44 | 74.73 | 10.48 |
| 8. | ባህርዳር | 2425.48 | 1525.36 | 62.89 | 2901.20 | 1323.60 | 45.62 | 2200.17 | 1629.98 | 74.08 |
| 9. | ሀበሻ | 1463.07 | 1816.84 | 124.18 | 2000.61 | 526.53 | 26.32 | 2682.00 | - | - |

**አባሪ 4**

**<u>መመዘኛ መስፈርቱ የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች</u>**

- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002
- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተገልጋዮች ቻርተር መጋቢት/2007 ዓ.ም/
- የ 2008 ዓ.ም የውጤት ተኮር እቅድ

- የ 2009 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር እቅድና የመልካም አስተዳደር እቅድ
- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የ 2008፣ 2009 እና 2010 በጀት ዓመታት እቅድ-አፈፃፀም ሪፖርቶች
- የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የ 2010 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር እቅድ
- የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ስትራቴጂክ እቅድ(2008-2012 ዓ.ም)
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995
- የአካባቢ ብክለት አዋጅ ቁጥር 300/1995
- ከኢንስቲትዩቱ ውጤት ተኮር እቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ
- Leather, Goods and Glove Factories Management and Technology Gaps Assessment and Analysis (የቆዳ ፣ የቆዳ ዕቃዎች እና ጓንት ፋብሪካዎች የአስተዳደር እና የቴክኖሎጂ ክፍተትን መገምገም እና መተንተን)
- እ.ኤ.አ ግንቦት 2017 የቆዳ ፋብሪካዎች የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ሪፖርት
- የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይት አዋጅ
- ነሀሴ 29/2009 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንዑስ ዘርፍ ያጋጠሙ ችግሮችን መፍታት በሚል የተፃፈ ደብዳቤ